**SIDAAMU DAGOOMU QOQQOWI MOOTIMMA AFFINI GAAZEEXA**

**የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት አፍኒ ጋዜጣ**

**SIDAAMA NATIONAL REGIONAL STATE AFFINI GAZETA**

5ki Diro Kiiro___

Hawaasa, Badheessa 8, 2017 M.D

Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Amaalete Mini Allaalshi Hundaanni Fulinoho

በሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

፭ኛ ዓመት ቁጥር______

ሀዋሳ መጋቢት ፰፣ ፳፻፲፯ ዓ.ም

**Amado**

**Wodhote Kiiro 49/2017**

SIDAAMU DAGOOMU QOQQOWI MOOTIMMA GORSU WAY OWAANTE WODHO…… QOOLA ….1

**Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Gorsu Way Owaante Wodho**

Mootimma, Mootimma ikkitinokkiti uurrinshubanna latishshu irkisaano fulonni ijaartino Gorsunna direenejete awutaare horammeyyete sayiisatenna owaantete shiqqo qorqorsha assate dandisiisanno sufinoha, farcotenna gummamo ikkino gorsu way horonshi seeru amuraate diriirsa hassiissanota ikkite leelitinohura;

Gorsunna direenejete awutaare annimatenni gashshitannore, agartanoorenna tuwatannore, gorsu waa horonsidhe baatonsa aaninni afi'nanni laalchonna laalchimma loossitano interpirayizootanna maamarra tantanantanno amanyoote diriirsa hasiissannota ikkite leeltinohura**;**

Sidaamu Dagoomi Qoqqowu Mootimma Gashshootu Amaale Mini Qoqqowu Bayriidi Seeri quwa 57 cinaancho quwa (6) nna Woyyaawinoha Qoqqowu Jefisiisano Bissa Uurrisate, Biilloonyenna Loosu Qeechansa Murate Fulino Lallawi kiiro 32/2015 quwa 10 cinaancho quwa (13) hunda uyinoonisi biilloonyi garinni tenne wodho fushshino.

**ማውጫ**

**ደንብ ቁጥር ፵፱/፳፻፲፯**

የሲዳማ ብሔራዊ ክልል መንግሥት የመስኖ ውሃ አገልግሎት ደንብ….. ገጽ….፩

**የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የመስኖ ውሃ አገልግሎት ደንብ**

በመንግሥት፤ መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶችና በልማት አጋሮች ወጪ የተገነቡ የመስኖና ድሬኔጅ አውታሮችን ለተጠቃሚዎች ለማስተላለፍ እና የአገልግሎት አቅርቦት ለመቆጣጠር የሚያስችል ዘላቂ፤ ፍትሀዊና ዉጤታማ የሆነ የመስኖ ዉሃ አጠቃቀም የሕግ ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የመስኖና ድሬኔጅ አዉታሮችን በባለቤትነት የሚያስተዳድሩ፣ የሚጠብቁና የሚንከባከቡ፤ የመስኖ ውሃን በመጠቀም ከማሳቸው የሚገኘውን ምርትና ምርታማነት የሚያሳድጉ ኢንተርፕራይዞች እና ማህበራት የሚደራጁበትን ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት መስተዳድር ምክር ቤት በክልሉ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 57 ንዑስ አንቀጽ (6) እና የክልሉን አስፈፃሚ አካላት ለማቋቋም፣ ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 32 አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ ( 13) ሥር በተሰጠዉ ሥልጣን መሰረት ይህንን ደንብ አዉጥቷል፡፡

AFFINI GAAZEEXI P.S.K …..
አፍኒ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. …..
Web address: www.affinigazet.gov.et

## GAFA MITE

## XAPHOOMU WORO

1. **Harancho Umo**

   Tenne wodho ‘’**Gorsu Way Owaante Wodho Kiiro 49/2017**’’ yine su’misa dandiinanni.

2. **Tiro**

   Qaalu eo wole tiro uyisiisanoha ikka hoogiro tenne wodho giddo:

   1) ‘’**Qoqqowoho**’’ yaa Sidaamu dagoomu qoqqowi mootimmati;
   2) ‘’**Biiro**’’ yaa Sidaamu dagoomu qoqqowi mootimma Way, Shiilotenna, Enerjete biiroti;
   3) ‘’**Ejense**’’ yaa Sidaamu dagoomu qoqqowi mootimma gorsu latishshi ejenseti;
   4) ‘’**Qorqoranno biso**’’ yaa qoqqowu gorsu latishshi ejense ikkitanna hasiishshu garinni zoonete woy woradu way, shiilotenna enerjete biddishsha woy borrote mine kamaalanno;
   5) ‘’**Bordete**’’ yaa gorsu way owaante interprirayize aliidimmatenni massagatenna gashshate tenne wodho garinni uurritinote;
   6) ‘’**Interpiraayize**’’ yaa gorsu way owaante aate uurritino interpiraayizeti;
   7) ‘’**Gorsu way afamanno bayicho**’’ yaa way kalaqamunnino ikko mannu loosino doogonni loosame corame afamanno baycho, baattote aaniidinna baattote woriidi waa, buicho, lagu waa, balete woy xeenu waanna babbaxxitino ragubbanni

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "**የመስኖ ውሃ አገልግሎት ደንብ ቁጥር ፵፱/፳፻፲፯**" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፤

   1) “**ክልል**” ማለት የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ነው፤
   2) “**ቢሮ**” ማለት የሲዲማ ብሔራዊ ክሌሊዊ መንግሥት ዉሃ፣ ማዕድንና ኢነርጂ ቢሮ ሆኖ የስር መዋቅሩን ይጨምራል፤
   3) “**ኤጀንሲ**” ማለት በሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ክልል የመስኖ ልማት ኤጀንሲ ነው፤
   4) “**ተቆጣጣሪ አካል**” ማለት የክልሉ መስኖ ልማት ኤጀንሲ ሲሆን እንደአግባቡ የዞን ወይም ወይም የወረዳ የውሃ፣ የማዕድንና ኤንርጂ መመሪያን ወይም ጽህፈት ቤትን የሚጨምር ነው፤
   5) ‘’**ቦርድ**’’ ማለት የመስኖ ውሃ አገልግሎት ኢንተርፕራይዝን በበላይነት እንዲመራና እንዲያስተዳድር በዚህ ደንብ መሰረት የተመሰረተ አካል ነው፤
   6) **ኢንተርፕራይዝ** ማለት የመስኖ ውሃ አገልግሎት ለመስጠት የተመሰረተ ኢንተርፕራይዝ ነው፤
   7) ‘’**የመስኖ ውሃ መገኛ ሥፍራ**’’ ማለት ውሃ በተፈጥሮም ሆነ በሰው ሰራሽ መንገድ ተሰርቶ ተጠራቅሞ የሚገኝበት ስፍራ፣ የገጸ ምድርና የከርሰ-ምድር ውሃ፣ የምንጭ፣ የወንዝ፣ የኩሬ ውሃ እና ከተለያዩ አቅጣጫዎች የሚፈስ

du‘‘namanno woy burqanno waati;

8) **‘’Gorsu way loossa’’** yaa baattote aaniidinna baattote woriidi waa afi‘‘rate, kofate woy way kuusamannowa loosate, baattote aananna baattote giddo way masmara diriirsate loonsanni loossa ikkite waa gorsaho hosiisa, kofa, uma, fiyaa, xiinxalla, qorqora, gashsha, bikka, hodhisa, saysa, maxinaamimma hoola, co‘‘ichimma agara, lolahe hoolannoha ijaarsanna woleno labbanno loossa jeefisa amaddanno;

9) **“Horaameessa’’** yaa gorsu way owaante horoonsi‘‘ranno mancho woy maamara woy interpiraayizeti;

10) **“Loosu Massagancho’’** yaa loosaasinetenna loosasinchu lallawinni diwantannokki loosu masaggaano yaano interpiraayizete loosu ha‘‘risaanchi, loosu ha‘‘rinshubba massagaanonna interpiraayizete manajimentete miilla amadanno;

11) **‘’Maamara’’** yaa tenne wodhonni tantanaminonna borreessamino gorsu way horaameeyye maamarati;

12) **‘’Gorsunna du’’namaanchu awutaare’’** yaa bikkantino baatto qarqarira gorsu waa hodhisate horote aana hossanno boye woy tubbote woy gorsu awutaare ikkitanna kuri ledo xaadooshshu noonsa aye way raga sorisiinsanniha, kofatto woy waa hoollanni wuqire, corranniha woy buicho hattono aye gorsu way sa’anno nafara, paampe, xaadissanno doogga, baatto, ijaarubba

ወይም የሚመነጭ ውሃ ነው፤

8) **“የመስኖ ውሃ ሥራዎች”** ማለት የገጸ-ምድርና የከርሰ-ምድር ውሃን ለማግኘት፣ ለማጠራቀም ወይም የውሃ ማጠራቀሚያ ለመስራት፣ የመሬት ላይና የመሬት ውስጥ የውሃ መስመር ለመዘርጋት የሚሰሩ ስራዎች ሆኖ፣ እንደ ውሃን ለመስኖ ማዋል፣ መገደብ፣ መቆፈር፣ መጥረግ፣ መቆጣጠር፣ማስተዳደር፣ ማጥናት፣ መለካት፣ ማጓጓዝ፣ ማስተላለፍ እና ሌሎች የመሳሰሉ ስራዎችን መፈጸምን ይጨምራል፤

9) **“ተጠቃሚ”** ማለት የመስኖ ውሃ አገልግሎት የሚጠቀም ሰው ወይም ማህበር ወይም ኢንተርፕራዝ ማለት ነው፤

10) **“የሥራ መሪ”** ማለት በሰራተኛና አሰሪ አዋጅ የማይሸፈኑ የሥራ መሪዎች ማለትም የኢንተርፕራይዙ ሥራ አስኪያጅ፣ የስራ ሂደቶች መሪዎች እና የኢንተርፕራይዙ ማኔጅመንት አባላትን ይጨምራል፤

11) **“ማህበር”** ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት የተደራጀና የተመዘገበ የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ማህበር ነው፤

12) **“የመስኖ እና ድሬኔጅ አውታር”** ማለት ወደ ተወሰነ መሬት አካባቢ የመስኖ ውሃን ለማጓጓዝ ጥቅም ላይ የሚውል ቦይ ወይም የቱቦዎች ወይም የመስኖዎች አውታር ሲሆን ከነዚሁ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ማንኛውንም የውሃ መጥለፊያን፣ ግድብን ወይም የውሃ ማገለያ ውቅርን፣ ማጠራቀሚያን ወይም ኩሬን እንዲሁም ማናቸውንም የመስኖ ውሃ መተላለፊያ በሮችን፣ ፓምፖችን፣ መጋቢ መንገዶችን፣ መሬትን፤

hattono gorsu awutaare direenejete ledo horota aana hosiisate, gatamarsate woy haroonsate hasiissano tantano baala kaamaltanno;

13) ‘’**Du’namaanchu awutaare**’’ yaa tirfe xeenu woy gorsu waa irshu giddonni fushshate loonsonni mannu loosino woy kalaqamu, qaranna beekkano booyenna xaadoshshu noonsa wuqiroota kamaalanno;

14) “**Qara gorsu du’namaanchi awutaare**” yaa lame woy hakku ale ikkitino maamara owaantete qoqqowubba gorsu waa hodhisate owaante uytano gorsunna du’namaanchu Awutaareeti;

15) ‘’**Yannite gorsu du’namaanchi awutaare**” yaa medebenya xiinxallonna dizaayne aana xintamme ijaarsinoonni woy yannite ikkitano gede assinoonni gorsu du’namaanchi awutaareeti;

16) “**Budu Gorsu Du’namaanchi Awutaare**” yaa rosichunni afi’noonni egenoonni qarqarunni afi’nanni uduuninni ijaarsinoonni gorsu du’namaanchi awutaareeti;

17) **“Ahad”** yaa mittu maamari owaantete qoqqowi giddo gama golaati;

18) “**Ahaadete woshshantannori**” yaa mitte ahaade riqiwe maamaru xaphoomu songo gaambooshi aana beeqqano gede doorantino miillati;

19) “**Xaphoomu songo”** yaa mittu maamari miilla woy ahaade riqiwaano hanqaffino

ህንፃዎችን እንዲሁም የመስኖ አውታሩን ከነድሬኔጁ ጥቅም ላይ ለማዋል፣ ለመጠገን ወይም ለማደስ አስፈላጊ የሆኑ ውቅሮችን ሁሉ ያካትታል፤

13) **“ድሬኔጅ አውታር”** ማለት ትርፍ የዝናብ ወይም የመስኖ ውሃን ከማሳ ለማስወገድ የተሰራ ሰው ሰራሽ ወይም ተፈጥሯዊ፣ ዋና እና መጋቢ ቦዮችንና ተያያዥነት ያላቸው ውቅሮች ነው፤

14) **“ዋና የመስኖና ድሬኔጅ አውታር”** ማለት ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ወደሆነ የማህበራት የአገልግሎት ክልሎች የመስኖ ውሃ ለማጓጓዝ የሚያገለግል የመስኖና ድሬኔጅ አውታር ነው፤

15) **“ዘመናዊ የመስኖና ድሬኔጅ አውታር”** ማለት በመደበኛ ጥናትና ዲዛይን ላይ በመመሥረት የተገነባ ወይም ዘመናዊ እንዲሆን የተደረገ የመስኖና ድሬኔጅ አውታር ነው፤

16) **“ባህላዊ የመስኖና ድሬኔጅ አውታር”** ማለት በልምድ በካበተ እዉቀትና በአካባቢ በሚገኝ ቁሳቁስ የተገነባ የመስኖና ድሬኔጅ አውታር ነው፤

17) **“አሀድ”** ማለት የአንድ ማህበር የአገልግሎት ክልል የተወሰነ ክፍል ነው፤

18) **“የአሀድ ተጠሪ”** ማለት አንድን አሀድ በመወከል በማህበሩ ጠቅላላ ጉባዔ ስብሰባ ላይ እንዲካፈል የተመረጠ አባል ነው፤

19) **“ጠቅላላ ጉባዔ”** ማለት የአንድ ማህበር አባላትን ወይም የአሀድ ተወካዮችን

aliidi massagaancho bisooti;

20) "**Loosu jeefisiisancho komite**" yaa mittu maamari loosi millimmo harunsanonna qorqorano gede xaphoomu songonni dooramino bisooti;

21) **Manchoho** yaa kalaqamu mancho woy seerunni mannimate qoosso uyinoonisi bisooti;

22) Tenne wodho giddo mitte koo/teemanni xawinsoonnihu wole koo/teemano kamaalanno.

**3. <u>Jeefishshu Mami-geeshsha</u>**

Tini wodho qoqqowu mootimma baajetenni ikko mootimmannita ikkitinokki uurrinshubba woxu irkonni qoqqowu giddo ijarsinoonni woy albillite ijaarsinanni gorsu xintu latishshubbanna daga horonsidhanno budu gorsu xintu latishshubba aana tantanantino gorsu waa horonsidhanno interpiraayizubbanna maamarra lainohunni loosu aana hossanno.

**4. <u>Wodhote Hexxo</u>**

1) Uurrinshubbate owaantete qoqqowi giddo afamanno gorsu du'namaanchi awutaare wo'munni wo'ma woy bocunni annimatenni gashshatenna massagate;
2) Ikkado ikkino gorsu way owaante dagate

ያቀፈ ከፍተኛ የውሣኔ ሰጪ አካል ነው፤

20)"**የሥራ አመራር ኮሚቴ**" ማለት የአንድ ማህበርን የሥራ እንቅስቃሴ እንዲከታተልና እንዲቆጣጠር በጠቅላላ ጉባዔ የተመረጠ አካል ነው፤

21)"**ሰው**" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፣

22) በዚህ ደንብ ውስጥ በወንድ ጾታ የተገለጸው ማንኛውም ቃል የሴት ጾታንም ይጨምራል፡፡

**3. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>**

ይህ ደንብ በክልሉ መንግስት በጀትም ሆነ መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች የገንዘብ ድጋፍ በክልሉ ውስጥ የተገነቡ ወይም ወደፊት በሚገነቡ የመስኖ መሠረተ ልማቶችና ህብረተሰቡ በሚጠቀምባቸው ባህላዊ የመስኖ መሠረተ ልማቶች ላይ የተደራጁ የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ኢንተርፕራይዞች እና ማህበራትን በሚመለከት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

**4. <u>የደንቡ አላማዎች</u>**

1) በተቋማት የአገልግሎት ክልል ውስጥ የሚገኘውን የመስኖና ድሬኔጅ አውታርን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በባለቤትነት የማስተዳደርና የመምራት፤
2) በቂ የሆነ የመስኖ ውሃ አገልግሎት ለህብረተሰቡ እንዲቀርብ ለማድረግ፤

shiqannoha assa;

3) Interepiraayizubbanna maamarra uminsa fulo owaantete afi"nanni eonni umonsa dandiite uminsaha ikkino baajetete amuraati hee"rennansa loossano gede assate;
4) Gorsu waa anfanni base agara, towaata, dafamate woy hafanfarretenni gargarate;
5) Dagate shiqqanno gorsu way owaante taalo ikkittinota, ikkadimmanna silanchimma nooseta ikkitano gede assa;
6) Way hafanfarenna daafama, bushshu hoshooshama gargarate maxinamimma ajishate, hattono qarqaru agarooshshenna amadooshshe harisate;
7) Waa suuqa lainohunni, garsu tekinoloojenna woyyaabbino giwirinnu loosu harinsho hayubba dhuka kaajjishate loossa loosantanno gede assatenna;
8) Hegeraamo gorsu way owaante aatenni qoqqowunnita dagomittetenna ikonoomete lopho jawaachishate.

**GAFA LAME**

**GORSU WAY OWAANTE INTERPIRAAYIZE**

**CINAANCHO GAFA MITE**

**INTERPIRAAYIZETE UURRA, BIILLOONYENNA LOOSU QEECHA**

3) ኢንተርፕራይዞች እና ማህበራት የራሳቸውን ወጪ ከአገልግሎት በሚገኘው ገቢ እራሳቸው ችለው የራሳቸው የሆነ የበጀት ሥርዓት ኖሯቸው እንዲሰሩ ለማድረግ፤

4) የመስኖ ውሃ መገኛ ቦታዎችን መጠበቅ፣ መንከባከብ ወይም ከብክነት ለመከላከል፤

5) ለህብረተሰቡ የሚቀርበው የመስኖ ውሃ አገልግሎት ፍትሀዊ ፣ ብቃትና ጥራት ያለው እንዲሆን ለማድረግ፤

6) የውሃ ብክነትንና ብክለትን፣ የአፈር መሸርሸርን የመከላከል፤ ጨዋማነትን የመቀነስ፣ እንዲሁም የአካባቢ ጥበቃና እንክብካቤን የማካሄድ፤

7) ስለውሃ ቁጠባ፤ ስለ መስኖ ቴክኖሎጂዎችና የተሻሻሉ የግብርና አሰራር ዘዴዎች የአቅም ግንባታ ስራዎችን እንዲከናወን የማድረግ፤ እና

8) ዘላቂነት ያለው የመስኖ ውሃ አገልግሎት በመስጠት የክልሉን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ለማፋጠን ነው፡፡

**ክፍል ሁለት**

**የመስኖ ውሃ አገልግሎት ኢንተርፕራይዝ**

**ንዑስ ክፍል አንድ**

**የኢንተርፕራይዝ መመስረት፣ ሥልጣንና ተግባር**

5. **Uurra**

1) Gorsu way owaante interpirаayize konni gedensaanni ‘’Interpiraayize’’ yaamante woshshantannoti tenne wodhonni urritino.
2) Konni quwi cinaancho quwa (1) garinni konni woroonni noo gorsu way owaante interpiraayizubba uminsa seeru mannima noonsare ikkite tenne wodhonni uurritino:
   (a) Hawaasi Gaangawi Woradi batinye qachuwi gorsu way owaante interpiraayize;
   (b) Wondo Genetete Woradi batinye qachuwi gorsu way owaante interpiraayize.
3) Konni quwira cinaancho quwa (2) worroonnihu noo gedeenni heerenna Ejense tenne wodhora quwa 6 worroonni safaraano garinni haaro interpiraayize uurrisa dandiitanno.
4) Konni quwi cinaancho quwa (1) garinni uurritino interpiraayize su‟mise albaanni ‟Gorsu Way Owaante Interpiraayize’’ yaanno su‟mishshi nooseta ikkitanna Ejensete borreessantu gedeensanni seeru mannima afi‟dhanno.
5) Ejense konni quwi cinaancho quwa (1) garinni Haaro interpiraayize uurrisuro interpiraayizete seeru mannima afamooshshu woraqata uuyitanno.

5. **መመስረት**

1) የመስኖ ውሃ አገልግሎት ኢንተርፕራይዝ ከዚህ በኂላ "ኢንተርፕራይዝ" ተብሎ የሚጠራ በዚህ ደንብ ተመስርቷል፡፡
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት የሚከተሉት የመስኖ ውሃ አገልግሎት ኢንተርፕራይዞች የራሳቸው ህጋዊ ሰውነት ያላቸው ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁመዋል፤
   (ሀ) የሃዋሳ ዙሪያ ወረዳ ብዝሀ-መንደር የመስኖ ውሃ አቅርቦት ኢንተርፕራይዝ፤
   (ለ) የወንዶ ገነት ወረዳ ብዝሀ-መንደር የመስኖ ውሃ አቅርቦት ኢንተርፕራይዝ፡፡
3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ኤጀንሲው በዚህ ደንብ አንቀጽ 6 የተመለከቱትን መስፈርቶች መሰረት በማድረግ አዲስ ኢንተርፕራይዝ ማቋቋም ይችላል፡፡
4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የተቋቋመው ኢንተርፕራይዝ ከስሙ በኃላ “የመስኖ ውሃ አገልግሎት ኢንተርፕራይዝ” የሚል ሐረግ ያለው ሲሆን በኤጀንሲው እንደተመዘገበ ሕጋዊ ሰውነት ያገኛል፡፡
5) ኤጀንሲው በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት አዲስ ኢንተርፕራይዝ ሲያቋቁም ለኢንተርፕራይዙ የሕግ ሰውነት የምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡

## 6. Interpiraayizete Safaraano

1) Aye interpiraayize konni woroonni noo safaraano kaima assatenni uurritannoha ikkanno:
   - (a) Interpiraayizete gorsu way horaameeyye batinye;
   - (b) Interpiraayizete gorsu way shiqo bikkanna ikkadimma;
   - (c) Interpiraayizete gorsu way tuqishshinna iillisha;
   - (d) Interpiraayizete gorsu way hafanfarre qorqorsha;
   - (e) Interpiraayize dirunni afidhanno eo bikki;
   - (f) Interpiraayizete noose gorsu way owaante fulo diwate wolqa;
   - (g) Interpiraayizete way owaante shiqo xurqa ikka;
   - (h) Interpiraayizete gorsu way horaameeyye batinye heekitarete;
   - (i) Lamu aleenni ikkitino danna xaaddanno lattino baatto amaddinoha ikkiro.
2) Konni quwi cinaanchu quwi (1) hunda worroonni safaraano kaima assatenni interpiraayizete aanino garinni deerru

## 6. የኢንተርፕራይዝ መስፈርቶች

1) ማንኛውም ኢንተርፕራይዝ በሚከተሉት መስፈርቶች ላይ በመመስረት የሚቋቋም ይሆናል፤
   - (ሀ) የኢንተርፕራይዙ የመስኖ የውሃ ተጠቃሚዎች ብዛት፤
   - (ለ) የኢንተርፕራይዙ የመስኖ የውሃ አቅርቦት መጠንና ብቃት፤
   - (ሐ) የኢንተርፕራይዙ የመስኖ ውሃ ሽፋንና ተደራሽነት፤
   - (መ) የኢንተርፕራይዙ የመስኖ የውሃ ብክነት ቁጥጥር፤
   - (ሠ) ኢንተርፕራይዙ በዓመት የሚያገኘው ገቢ መጠን፤
   - (ረ) ኢንተርፕራይዙ ያለው የመስኖ ውሃ አገልግሎት ወጪዎችን የመሸፈን አቅም፤ እና
   - (ሰ) የኢንተርፕራይዙ የመስኖ ውሃ አገልግሎት አቅርቦት ውስብስብነት፤
   - (ሸ) የኢንተርፕራይዙ የመስኖ የውሃ ተጠቃሚዎች ብዛት በሄክታር፤
   - (ቀ) ከሁለት በላይ የሆኑ በኩታ ገጠም የለማ ማሳ የያዘ ከሆነ፡፡
2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ስር የተደነገጉትን መስፈርቶች መሰረት በማድረግ ለኢንተርፕራይዝ እንደሚከተለው ደረጃ

fulinose:

(a) Umikki deerra;

(b) Layinki deera;

(c) Sayikki deerra.

3) Konni quwi cinaancho quwa (1) nna (2) garinni gorsu way owaante interpiraayize uurrinshu deerase konni woroonni noo garinni sasu deerinni gaamantanno:

(a) Deerra mitte 1000 heekitaare baatto aleenni dibbannota ikkituro;

(b) Deerra lame 500 kayise 999.9 geeshshi heekitaare baatto dibbannota ikkituro;

(c) Deerra sase 200 kayise 499.9 geeshshi heekitaare baatto dibbannota ikkituro.

**7. Hundaanchimma**

Gorsu way owaante interpiraayize hundaanchimma konni woroonni noohu garinni ikkitanno:

1) Umikki deerrira gaamantanno gorsu way owaante interpiraayize lame zoonenna hakunni aleenni ikkitino owaatamaano heedhusero hundaanchimmase Ejensete ikkitanno.

2) Mitte Zoone giddo calla owaante uytannota ikkituro hundaanchimmase zoonete gashshootu borro minira ikkitanno.

ወጥቶለታል፤

(ሀ) አንደኛ ደረጃ፣

(ለ) ሁለተኛ ደረጃ፣

(ሐ) ሶስተኛ ደረጃ።

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) መሰረት የመስኖ ውሃ አገልግሎት ኢንተርፕራይዝ ተቋማዊ ደረጃ በሚከተለው መልኩ በሶስት ደረጃዎች ይመደባል፤

(ሀ) ደረጃ አንድ ከ 1000 ሄክታር ማሳ በላይ የሚሸፍን ከሆነ፤

(ለ) ደረጃ ሁለት ከ500 እስከ 999.9 ሄክታር ማሳ የሚሸፍን ከሆነ፤

(ሐ) ደረጃ ሦስት ከ200 እስከ 499.9 ሄክታር ማሳ የሚሸፍን ከሆነ።

**7. ተጠሪነት**

የስኖ ውሃ አገልግሎት ኢንተርፕራይዝ ተጠሪነት ከዚህ እንደሚከተለው ይሆናል፤

1) በደረጃ አንድ የሚፈረጅ የመስኖ ዉሃ አገልግሎት ኢንተርፕራይዝ ሁለት ዞንና ከዛ በላይ ተገልጋይ ካለው ተጠሪነቱ ለኤጀንሲው ይሆናል፤

2) በአንድ ዞን ውስጥ ብቻ አገልግሎት የሚሰጥ ከሆነ ተጠሪነቱ ለዞን አስተዳደር ጽ/ቤት ይሆናል፤

3) Gorsu way owaante interpiraayize mittu woradira calla owaante uytannota ikkituro hundaanchimmase woradu gashshootu borro minira ikkitanno.
4) Mittu woradi aleenni owaante uytannoha ikkiro hundaanchimmase rooriidi horaameeyye noo woradu gashshooti borro minira ikkitanno.

**8. Interpiraayizete Biilloonyenna Loosu Qeecha**

Interpiraayizete konni woroonni noo biilloonyinna loosu qeechi heerannose:

1) Gorsu way poolise, istirateeje, pirograamenna seerubba loosu aana hosiissanno;
2) Deerrasi agarinoha, ikkado gorsu waa dagate shiqishshanno;
3) Uytanno owaante halashshate babbaxxitino eote bu''a hassanno, hasiishshu garinni gorsu way owaante investmentete fulo dagoomunni irkisantano gede jawaachishshanno;
4) Gorsu way owaante xa''ranno mannira gadadisanno richi xaada hoogiro xa''monsa aante garinni gorsu way doogo diriirsitanno, gatamartanno, halashshitanno, sheemate e''anno, haaronsitanno, woyyeessitannonna

3) የመስኖ ዉሃ አገልግሎት ኢንተርፕራይዝ በአንድ ወረዳ ብቻ አገልግሎት የሚሰጥ ኢንተርፕራይዙ ተጠሪነቱ ለወረዳዉ አስተዳደር ጽ/ቤት ይሆናል፤
4) ከአንድ ወረዳ በላይ አገልግሎት የሚሰጥ ከሆነ ተጠሪነቱ አብዛኛዉ ተጠቃሚ ያለበት ወረዳ አስተዳደር ጽ/ቤት ይሆናል፡፡

**8. የኢንተርፕራይዝ ሥልጣንና ተግባር**

ኢንተርፕራይዙ የሚከተለው ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል፤

1) የመስኖ ውሃ ፖሊሲ፣ ስትራተጂ፣ ፕሮግራሞች እና ህጎችን ሥራ ላይ ያውላል፤
2) ደረጃውን የጠበቀ፣ በቂ እና አስተማማኝ የመስኖ ውሃን ለህብረተሰብ ያቀርባል፤
3) የሚሰጠውን አገልግሎት ለማስፋፋት የተለያዩ የገቢ ምንጮችን ያፈላልጋል፤ እንዳስፈላጊነቱ የመስኖ ውሃ አገልግሎት የኢንቨስትመንት ወጪ በህብረተሰቡ እንዲደገፍ ያበረታታል፤
4) የመስኖ ውሃ አገልግሎት ለሚጠይቁ ሰዎች አስገዳጅ ሁኔታ ካላጋጠመ በስተቀር በጥያቄያቸው ቅደም ተከተል መሰረት የመስኖ ውሃ መስመር ይዘረጋል፤ ይጠግናል፤ ያስፋፋል፤ውል ይፈጽማል፤

sheemaate murtanno;

5) Ikkonoomete wolqa anje noonsa mannootira liqoote woy wole injiitanno doogganni gorsu waa eesidhanno gede irkissanno, jeefishshu fulanno biddisinni gumulamannoha ikkanno;

6) Uynanni gorsu way owaante shiqora seeru gumulonni baatooshshe yannatenni batisiissanno, gamba assitanno, gamba assinanni gedeno assitanno;

7) Owaantetenna hirote baatooshshe owatamaanote baatate wolqa mereersha assatenni yanna yannatenni xiinxallatenni Biirote widoonni boordete shiqeenna gumulamanno gede assitanno, gumulirono loosu aana hosiissanno;

8) Xiinxallote bandoonni gorsu way heeʼʼranno darga albillitete owaantera interpiraayizete suʼʼminni maarekkantenna ayirrite keeshshitanno gede hajo laʼʼannonsa bissa ledo sheemate eʼʼanno;

9) Haaro gorsu way shiqo xiinxalatenni bordete shiqishanno, fajjinirono loosu aana hosiissanno;

10) Gorsu Way afamanno dargubba qorobbe amaddanno; daafamme gargartanno;

11) Eʼʼino sheemaati garinni gorsu waa

ያድሳል፤ ያሻሽላል፤

5) የኢኮኖሚ አቅም ውስንነት ያለባቸው ሰዎች በብድር ወይም በሌሎች አመቺ መንገዶች የመስኖ ውሃ እንዲያስገቡ ይደግፋል፤ አፈጻጸሙ በሚወጣው መመሪያ የሚወሰን ይሆናል፤

6) ለሚሰጠው የመስኖ ውሃ አገልግሎት አቅርቦት በህግ የተወሰነውን ክፍያ በወቅቱ ያስከፍላል፤ ይሰበስባል፤ እንዲሰበሰብ ያደርጋል፤

7) የአገልግሎትና ሽያጭ ታሪፍን የተጠቃሚዎችን የመክፈል አቅም ማዕከል በማድረግ በየጊዜው በማጥናት በቦርዱ በኩል ለቢሮው ቀርቦ እንዲወሰን ያደርጋል፤ ሲወሰንም ሥራ ላይ ያውላል፤

8) በጥናት የተለዩ የመስኖ ውሃ መገኛ ስፍራዎች ለወደፊት አገልግሎት በኢንተርፕራይዙ ስም ተመዝግበውና ተከብረው እንዲቆዩ ጉዳዩ ከሚመለከተው አካል ጋር ስምምነት ይፈጽማል፤

9) አዳዲስ የመስኖ ውሃ አቅርቦት ዘዴዎችን በማጥናት ለቦርዱ ያቀርባል፤ ሲፈቀድም ስራ ላይ ያውላል፤

10) የመስኖ ውሃ መገኛ ቦታዎችን ይንከባከባል፤ ይጠብቃል፤ ከብክለት ይከላከላል፤

horonsidhe baatooshshe baattinokki mannooti aana seeru qaafo adhitanno woy adhinanni gede assitanno;

12) Loosaasinete agarama hasiisanno babbaxitino horo xiinxallenni bordete shiqishshanno, kaajiturono loosu aana hosiissanno;

13) Gorsu way loossa irkissanno garinni hojjinni woy wolootu uurrinshuwa ledo ikkatenni latishshu loossa aana beeqqitara dandiitanno;

14) Loosase gumaame assate gama loosose harancho woy seeda yanna sheematinni seerunni buuxamino dandoo noosi bisira uytara dandiitanno;

15) Jajju anna ikkitanno, sheemmaate e’’anno, qaxxartanno, qaxxarantanno;

16) Hexxo gafa gansiisate kaa’’litannore wole kuri labbanno loosu qeechuwa loossanno.

**9. Interpiraayizete Afaamooshshu Woraqata Aanna Egensiisa**

1) Ejense tenne wodho garinni uurritino uurrinshshara woy haaro uurrinshshara uurrinshshate su’’ma, noo deerranna

11) በገቡት ውል መሰረት የመስኖ ውሃን ተጠቅመው ክፍያ ባልፈጸሙ ሰዎች ላይ ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል ወይም እንዲወሰድባቸው ያደርጋል፤

12) ለሰራተኞች ሊጠበቁ የሚገባቸው የተለያዩ ጥቅማ ጥቅሞችን አጥንቶ ለቦርድ ያቀርባል፤ ሲፀድቅም ስራ ላይ ያውላል፤

13) የመስኖ ውሃ ስራዎችን በሚደግፍ መልኩ በግል ወይም ከሌሎች ድርጅቶች ጋር በመሆን በልማት ስራዎች ላይ ሊሳተፍ ይችላል፤

14) ሥራውን ውጤታማ ለማድረግ የስራውን የተወሰነውን ክፍል በአጭር ወይም በረጅም ጊዜ ውል በህግ የተረጋገጠ ችሎታ ላለው አካል ሊሰጥ ይችላል፤

15) በስሙ ንብረት ያፈራል፤ ስምምነት ይገባል፤ ይከሳል፤ ይከሰሳል፤

16) ዓላማዎቹን ከግብ ለማድረስ የሚረዱት ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል።

**9. ለኢንትርፕራይዙ የምስክር ወረቀት መስጠት እና ማስተዋወቅ**

1) ኤጀንሲው በዚህ ደንብ መሰረት ለተቋቋመው ኢንተርፕራይዝ ወይም አዲስ ኢንተርፕራይዝ የኢንተርፕራይዙን ስም፣ ያለበትን ደረጃ እና የወጣበትን ቀን

fultino barra xawisanno afamooshshu woraqata qixxeesite uytanno.

2) Ejense konni quwi cinaanchu quwi (1) garinni deerra uuyituro hala‟ladu tuqishshi noosi qoqqowunna gobbate deerri gaazeexi aana atansiisatenni dagate egensiisa noose.

3) Konni quwi cinaanchu quwi (2) hunda worroonnihu noo gedeenni ejense tenne wodhonni quwa 4 cinaancho quwa (2) garinni uurritanno haaro uurrinshshara deera uytano woyte hasiishshu garinni borrote egensiissanno.

## CINAANCHO GAFA LAME

## INTERPIRAAYIZETE GASHSHOOTU BISSA

### 10. Tantano

Aye interpiraayize konni woroonni noo tantano heedhannose:

1) Borde;
2) Loosu harisanchi; nna
3) Hasiisano loosaasine.

### 11. Bordete Uurranna Hundaanchimma

1) Interpiraayize aliidimmatenni massagganno borde, konni gedensaanni "borde"" yine woshshinanniti tenne

የሚገልጽ የምስክር ወረቀት አዘጋጅቶ ይሰጣል፡፡

2) ኤጀንሲው በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት የምስክር ወረቀት ሲሰጥ ሰፊ ሽፋን ባለው የክልል እና የሀገር አቀፍ ጋዜጣ ላይ በማሳተም ለህዝብ ማሳወቅ አለበት፡፡

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ስር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ኤጀንሲው በዚህ ደንብ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ (2) መሰረት ለሚቋቋም አዲስ ኢንተርፕራይዝ የምስክር ወረቀት ሲሰጥ እንደአስፈላጊነቱ በደብዳቤ ይገልፃል፡፡

## ንዑስ ክፍል ሁለት

## የኢንተርፕራይዙ የአስተዳደር አካላት

### 10.አደረጃጀት

ማንኛውም ኢንተርፕራይዝ የሚከተለው አደረጃጀት ይኖረዋል፤

1) ቦርድ፤
2) ሥራ አስኪያጅ፤ እና
3) አስፈላጊ ሠራተኞች፡፡

### 11. የቦርዱ ምስረታ እናተጠሪነት

1) ኢንተርፕራይዙን በበላይነት የሚመራ ቦርድ፣ ከዚህ በኋላ "ቦርድ" ተብሎ የሚጠራ፣ በዚህ ደንብ ተመስርቶዋል፤

wodhonni uurritino.

2) Bordete hundaanchimma tenne wodhora quwa 7 cinaancho quwa (1) kayise (4) geeshsha worroonnihu garinni ikkitano.

**12. <u>Bordete Miilla</u>**

1) Deerra mittoho gaamantannonna lame zoonennaa hakuyi aleenni owaante uuyitannori hundaanchimmansa Ejensete ikkitinori:
   - (a) Ejensete sooreessi...Gambisaancho;
   - (b) Zoonete xintu latishshi sooreessi………Miila
   - (c) Meentu, Wedellunna Dagoomu Hajo biddishshi sooreette…………..Miila;
   - (d) Saadate jiro latishshi Biddishshi sooreessi……………………….Miila;
   - (e) Elekitiriikete Owaante Wodiidi Riiginete sooreessi…………….Miila;
   - (f) Horaameyete woradda gashshaano……………………..Miila;
   - (g) Horaamesu woradi way, shiilotenna enerjete borro mini sooreessi…….............................Miila;
   - (h) Horaamesu woradi Giwirinnu borro mini sooreessi……..................Miila;
   - (i) Horaamesu woradi loosu kalaqo borro mini sooreessi…….................Miila;
   - (j) Interpiraayizete loosu harisaanchi………Huuro aannokki miila;

2) የቦርዱ ተጠሪነት በዚህ ደንብ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ (1) እስከ (4) ድረስ በተደነገገው መሰረት ይሆናል፡፡

**12.<u>የቦርድ አባላት</u>**

1) በደረጃ አንድ የሚፈረጁ እና ሁለት ዞን እና ከዛ በላይ አገልግሎት የሚሰጡ ተጠሪነታቸው ለኤጀንሲው የሆኑ፤

(ሀ)የኤጀንሲው ኃላፊ…………………..ሰብሳቢ፤

(ለ)የዞኑ የመሠረተ ልማት ሀላፊ………..አባል፤

(ሐ) የሴቶች፣ ወጣቶች እና ማህበራዊ ጉዳይ መምሪያ ሀላፊ…..አባል፤

(መ) የእንስሳት ሀብት ልማት መምሪያ ኃላፊ…………………………………….…አባል፤

(ሰ) የኤሌክትሪክ አገልግሎት የደቡብ ሪጂን ሀላፊ…………………………………..አባል፤

(ረ) የተጠቃሚ ወረዳ አስተዳዳሪዎች…..አባል፤

(ሠ) የተጠቃሚ ወረዳ ው/ማ/ኢነርጂ ጽ/ቤት ኃላፊ………….አባል፤

(ሽ)የተጠቃሚ ወረዳው ግብርና ፅ/ቤት ኃላፊ……………………………………..አባል፤

(ቀ) የተጠቃሚ ወረዳው የስራ ዕድል ፈጠራ ፅ/ቤት ኃላፊ-------------------------------- አባል፤

(በ)የኢንተርፕራይዙ ሥራ አስኪያጅ----አባል (ድምጽ አልባ)

(k) Interpiraayizete loosu harisaanchinni riqiwamannohu….. Huuro aannokki borreesancho ikkanno.

2) Mitte zoone giddo calla owaante uuyitannonna hundaanchimansa zoonete gashshooti borro minira ikkitinori:

(a) Zoonete qaru gashshaanchi………..Gambisaancho;

(b) Zoonete xintu latishshi Biddishshi sooreessi……Layinkki gambisaancho;

(c) Meentu, Wedellunna Dagoomu Hajo biddishshi sooreette…………..Miila;

(d) Saadate Latishshi Biddishshi sooreessi……………………..Miila;

(e) Elekitiriikete Owaante Wodiidi Riiginenni riqiwamano mittu manchi………………………….Miila;

(f) Horaamesu woradi gashshaano…………………….Miila;

(g) Horaamesu woradi way, shiilotenna enerjete borro mini sooreessi……………………….Miila;

(h) Horaamesu woradi loosu kalaqo borro mini sooreessi…………Miila;

(i) Horaameessu woradi Giwirinnu Borro Mini Sooreessi………………….Miila;

(j) Interpirayizete loosu harisaanchi……Huuro aannokki miila;

(k) Interpirayizete loosu harisaanchinni riqiwamannohu….. Huuro aannokki borreesancho ikkanno.

(ተ) በኢንተርፕራይዙ ሥራ አስኪያጅ የሚመደብ ጸሐፊ----------------- አባል (ድምጽ አልባ)፡፡

2) በአንድ ዞን ውስጥ ብቻ አገልግሎት የሚሰጥ እና ተጠሪነቱ ለዞኑ አስተዳደር ጽ/ቤት የሆነ፤

(ሀ)የዞኑ ዋና አስተዳዳሪ……ሰብሳቢ

(ለ)የዞኑ መሰረተ ልማት መምሪያ ሀላፊ………………………ምክትል ሰብሳቢ፣

(ሐ) የሴቶች፣ ወጣቶች እና ማህበራዊ ጉዳይ መምሪያ ሀላፊ………………………..አባል፣

(መ)የእንስሳት ሀብት ልማት መምሪያ ኃላፊ…………………………………አባል፤

(ሠ) የኤሌክትሪክ አገልግሎት በደቡብ ሪጂን የሚወክል አንድ ሰው………………አባል፤

(ረ)የተጠቃሚ ወረዳ አስተዳዳሪዎች………………………...አባል፣

(ሰ) የተጠቃሚ ወረዳ ው/ማ/ኢነርጂ ጽ/ቤት ኃላፊ…………………………………አባል፤

(ሸ) የተጠቃሚ ወረዳ ግብርና ጽ/ቤት ኃላፊ…………………..አባል፤

(ቀ) የተጠቃሚ ወረዳ የስራ ዕድል ፈጠራ ፅ/ቤት ኃላፊ-------------------------- አባል፤

(በ)የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ----አባል (ድምጽ አልባ)

(ተ) በድርጅት ሥራ አስኪያጅ የሚመደብ ጸሐፊ----------------- አባል (ድምጽ አልባ)፡፡

3) Mittu woradi giddo mittu ollii aleenni owaante uyitanorinna hundaanchimansa woradu gashshooti borro minira ikkitinori bordete miilla:
   (a) Woradu Qaru gashshaanchi…………Gambisaancho;
   (b) Giwirinnu borro mini sooreessi………………………Miila;
   (c) Way, shiilotenna enerjete borro mini sooreessi……………………….Miila;
   (d) loosu kalaqo borro mini sooreessi……………................Miila;
   (e) Meentu, Wedellunna Dagoomu Hajo borrote mini sooreette……….Miila;
   (f) Saadate latishshi borro mini sooreessi……………………….Miila;
   (g) Elekitriikete Owaante wodiidi qoqqowinni riqiwamanno 1 manchi………..……………..Miila;
   (h) Gorsu way horaameeyye maamarra 2 riqiwaano………………………Miila;
   (i) Interpirayizete loosu harisaanchi……Huuro aannokki miila;
   (j) Interpirayizete loosu harisaanchinni riqiwamannohu….. Huuro aannokki borreesancho ikkanno.

4) Dagoomunni dooramanno boordete miili loosu yanna sase diro ikkitanna aliidi loosu jeefishsha mareekisisiro kayinni ledote mite doyichora calla wirro

3) በአንድ ወረዳ ውስጥ ከአንድ ቀበሌ በላይ አገልግሎት የሚሰጡና ተጠሪነታቸው ለወረደ አስተዳደር ጽ/ቤት የሆኑ የቦርድ አባላት፤
   (ሀ) የወረዳው ዋና አስተዳዳሪ………ሰብሳቢ፤
   (ለ)የግብርና ፅ/ቤት ኃላፊ……………አባል፤
   (ሐ)የውሃ ማዕድንና ኢኔርጂ ፅ/ቤት ኃላፊ…………………………………አባል፤
   (መ)የስራ ዕድል ፈጠራ ፅ/ቤት ኃላፊ…አባል፤
   (ሠ)የሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶች ፅ/ቤት ኃላፊ……………………………………..አባል፤
   (ረ) የእንስሳት ሀብት ልማት ጽ/ቤት ኃላፊ…………………………………አባል፤
   (ሠ) የኤሌክትሪክ አገልግሎት ደቡብ ሪጂን የሚወከል አንድ ሰው……………….. አባል፤
   (ሽ)የመስኖ ውሃ ተጠቃሚ ማህበራት 2 ተወካዮች……………………………አባል፤
   (ቀ)የኢንተርፕራይዙ ሥራ አስኪያጅ-- አባል (ድምጽ አልባ)፤
   (በ)በኢንተርፕራይዙ ሥራ አስኪያጅ የሚመደብ ጸሐፊ----- አባል (ድምጽ አልባ)፡፡

4) ከማህበረሰቡ የሚመረጥ የቦርድ አባል የስራ ዘመን ሶስት አመት ሲሆን ከፍተኛ አፈፃፀም ካስመዘገበ ደግሞ ለተጨማሪ አንድ ዙር ብቻ

dooramara dandaanno.

5) Loososi garunni loosinokki bordete miili aye yannara borde keente miilomitetenni kayisatenni loosu mininni wole manna lekkisanno.

6) Konni quwi cinaancho quwa (5) garinni mittu bordete miili miilomitetenni kainohu huno loosenna ikkiro, garimma noosi seerinni xa‟mamannoha ikkanno.

**13. <u>Boordete Gambooshshu Amanyoote</u>**

1) Bordete gambooshshe sasu aganinni mitte hinge assinanniha ikkanna bordete gambisaanchi hasiishshu garinni winaamu gambooshshe woshshara dandaanno.
2) Gambooshshu aana lame sayikiha ikkitanno bordete miilla leelturo gambooshshunniha wo‟‟ma songo ikkitanno.
3) Konni quwira cinaancho quwa (2) garinni wo‟‟ma songo ikka hooguro aananno gambooshshi aana bocuna hakuyi ali miilla afanturo gambooshshe harisa dandiinanni.
4) Bordete gumulo gambooshshu aana leeltinorinni rooridi huuronni kaajjitannoha ikkana miillate huuro taalo ikkitura gambisaanchu irkisino hedo bordete gumulo ikkitanno.
5) Bordete gambooshshu ajandi lamu barri

በድጋሚ ሊመረጥ ይችላል፡፡

5) ስራውን በአግባቡ ያልተወጣ የቦርድ አባል በማንኛውም ጊዜ ቦርዱ ገምግሞ ከአባልነት በማንሳት ከመ/ቤቱ ውስጥ ሌላ ሰው ይተካል፡፡

6) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) መሠረት አንድ የቦርድ አባል ከአባልነት የተነሣው ጥፋት ፈፅሞ እንደሆነ፣ አግባብነት ባለው ሕግ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

**13.<u>የቦርዱ ስብሰባ ሥነ-ሥርዓት</u>**

1) የቦርደ ስብሰባዎች በየሶስት ወሩ አንድ ጊዜ የሚደረጉ ሲሆን የቦርደ ስብሳቢ እንደ አስፈላጊነቱ አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላ፡፡
2) በስብሰባው ላይ ሁለት ሶስተኛ የሚሆኑት የቦርድ አባላት ከተገኙ የስብሰባው ምለአተ ጉባኤ ይሆናል፡፡
3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሰረት ምለአተ ጉባኤ ካልሞላ በሚቀጥለ ስብሰባ ላይ ግማሽና ከዚያ በላይ አባላት ከተገኙ ስብሰባውን ማካሄድ ይቻላል፡፡
4) የቦርደ ውሳኔ በስብሰባው ላይ በተገኙ በአብላጫ ድምፅ የሚፀድቅ ሲሆን የአባላት ድምፅ እኩል ከሆነ በሰብሳቢው የተደገፈው ሀሳብ የቦርድ ውሳኔ ይሆናል፡፡
5) የቦርድ ስብሰባ አጀንዳ ከሁለት ቀናት በፊት በኢንተርፕራይዙ ዋና ስራ አስኪያጅ በኩል ለአባላቱ መቅረብ

albaanni interpirayizete qaru loosu harisaanchi widoonni miillate shiqa noosi.

6) Bordete miilla interpirayizete wolqa aana xintamatenni hasiishshu garinni owaantete barru hoshsho afi"dhara dandiitanno; tittirshu jeefishsha Biiro biddisunni gumultanno.

7) Konni quwi cinaancho quwa (1) kayise (4) geeshsha noohu noo gedeenni heerenna borde umise gambooshshu amanyoote galtinote wodhonni gumultara dandiitanno.

**14. <u>Bordete Biilloonyenna Loosu Qeecha</u>**

Boordete aane noo biilloonyinna loosu qeechi hee"rannose:

1) Interpirayize aliidimmatenni massaggannonna qorqortanno;
2) Interpirayizete qixxaabbe shiqqannose loosunna beejettete mixo xiinxallite gumultanno, loosu aana hosase illaallisanno;
3) Interpirayizete loosunna baajettete jeefishshu ripoorte keentanno, raga wortanno, hundaancho ikkitino bisira ripoorte shiqishshanno;
4) Daga hasaawisatenni yannite, xawaadonna lifinxe noosi loosu harinsho diriirsatenni loosu aana hosano gede assitanno;
5) Kaajado jajju, faynaansetenna mannu wolqa gashshooti qorqorshi amuraati heerasi buuxxanno, jeefishsha harunsitanno, shiqano odiitete guma

አለበት፤

6) ቦርድ አባላት በኢንተርፕራይዙ አቅም ላይ በመመስረት እንደ አስፈላጊነቱ የአገልግሎት አበል ሊያገኙ ይችላል ይሄንን በተመለከተ ቢሮው የአፈጻጸም መመሪያ ያወጣል፡፡

7) በዚህ አንቀፅ ከንኡስ አንቀጽ (1) እስከ (4) ያለው እንደተጠበቀ ሆኖ ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት በመተዳደሪያ ደንብ ሊወስን ይችላል፡፡

**14.<u>የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር</u>**

ቦርዱ የሚከተለው ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል፡

1) የኢንተርፕራይዙን ተግባራት በበላይነት ይመራል፤ ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤
2) በኢንተርፕራይዙ ተዘጋጅቶ የሚቀርብለትን የስራና በጀት ዕቅድ መርምሮ ያጸድቃል፤ ሥራ ላይ መዋሉንም ይከታተላል፤
3) የኢንተርፕራይዙን የስራና በጀት አፈጻጸም ሪፖርት ይገመግማል፤ አቅጣጫ ያስቀምጣል፤ ተጠሪ ለሆነለት አካል ሪፖርት ያቀርባል፤
4) ሕብረተሰቡን በማወያየት ዘመናዊ፣ ግልጸኝነት እና ቅልጥፍና ያለው አሰራር በመዘርጋት ስራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤
5) ጠንካራ የንብረት፣ የፋይናንስ እና የሰው ሀይል አስተዳደር ቁጥጥር ሥርዓት መኖሩን ያረጋግጣል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤ የሚቀርበውን የኦዲት ውጤት በማየት

la’atenni raga wortanno;

6) Innterpirayizete lophoranna halashimmara kaa’litanno addi addi woxunna jirote bu’a hansanni gede assitanno; jeefishsha harunsitanno;
7) Interpirayize xiinxallite shiqishannose gorsu way owaante taarife buuxxe kaajishanno; ripoorte Ejensete shiqishanno;
8) Wiinamu hajo xaadduro, urrinshunni shiqqannosi gobbate giddonna gobbate gobbaaydi wiinamu hirote xa‟‟mo la’’atenni hiro jeefantanno gede gumultanno;
9) Interpirayizete tantano gumultanno, loosu massagaanonna loosaasinete damooza, hattono barru hoshshonna addi addi horo xa‟‟mo buuxo assite gumulo sayissanno;
10) Interpirayizete loosu harisancho qaxarate, soorrote woy lophote gaamate loosoho hasiisanno rosichonna ikkadima noonsa heewisamaano giddo hewisiisse dooratenni deerrinsa aante garinni biirote woy biirote tantano shiqishatenni kajishiishanno, jeefishshu fulanno biddisinni gumulamannoha ikkanno.
11) Interpirayizete loosu harisanchinna loosaasine gadachonsa garunni fulansa illaallisanno, qorqortanno;
12) Interpirayizete loosu harisanchi aana seeru garinni qaafo adhitanno.

አቅጣጫ ያስቀምጣል፤

6) ለኢንተርፕራይዙ እድገትና መስፋፋት የሚረዱ የተለያዩ የገንዘብና ሀብት ምንጮች እንዲፈለጉ ያደርጋል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤
7) በኢንተርፕራይዙ ተጠንቶ የሚቀርብለትን የመስኖ ውሃ አገልግሎት ታሪፍ መርምሮ ያፀድቃል፤ ሪፖርት ለኤጀንሲው ያቀርባል፤
8) አስቸኳይ ጉዳይ ሲያጋጥም፣ በኢንተርፕራይዙ የሚቀርብለትን የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር አስቸካይ ግዢ ጥያቄ በመመልከት የግዢው እንዲፈጸም ይወስናል፤
9) በኢንተርፕራይዙን መዋቅር ያጸድቃል፤ የሥራ መሪዎችና ሠራተኞች ደመወዝ፣ እንዲሁም አበልና የጥቅማጥቅም ጥያቄዎችን እየመረመረ ውሳኔ ይሰጣል፣
10) የኢንተርፕራይዙን ሥራ አስኪያጅ ለመቅጠር፣ በዝውውር ወይም በዕድገት ለመመደብ ለስራው የሚያስፈልገውን ልምድና ችሎታ ካላቸው ዕጩዎች ውስጥ አወዳድሮ በመምረጥ በደረጃቸው ቅደም ተከተል መሰረት ለቢሮው ወይም ለቢሮው መዋቅር በማቅረብ ያስጸድቃል፤ አፈጻጸሙ በሚወጣው ደንብ የሚወሰን ይሆናል፤
11) የኢንተርፕራይዙ ሥራ አስኪያጅ እና ሰራተኞች ግዴታቸውን በአግባቡ መወጣታቸውን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤
12) በኢንተርፕራይዙ ሥራ አስኪያጅ ላይ በህጉ መሰረት እርምጃ ይወስዳል።

**15. <u>Bordete Miilla Xa'mamooshshe</u>**

1) Bordete miilla tenne wodho kaiminni uynoonninsa yawo fula hoogansanni kainohunni uurrinshate iillitanno gawajjora hojji hojjinna gutu xa"mamishshi hee"rannonsa.
2) Konni quwira cinaancho quwa (1) hunda worroonnihu hee"rirono, boordete gumulo uyinanni yannara gumulo giwatenni huurote baxxino bordete miili gumulo abitanno xa"mamoshinni fayyo ikkanno gede hedosi borreesatenni malaatisa noosi.
3) Konni quwira cinaancho quwa (1) hunda worroonnihu noo gedeenni, mittu bordete miili hasi"nanni garinni yawosi fula hoogiro biiro woy biirote tantano aye yannara seeru garinni taashshote qaafo adhitasira woy miilimatenni kayisatenni wole manna wortara dandiitanno.

**<u>CINAANCHO GAFA SASE</u>**

**<u>LOOSU HARISAANO GASHSHOTU AMURAATE(FILA(QIXIRE) NNA GAMOOSHSHU AMURAATE)</u>**

**16. <u>Loosu Harisaanchi Qixire woy Gaamooshshenna Hundaanchimma</u>**

1) Borde biiro interpiraayizete qara loosu harisaancho qaxarate woy gaamate fushshitanno biddisira xawinsoonni safaraano garinni loosu gumaamimmara hasiisano mancho filte hewisiisatenni

**15.<u>የቦርድ አባላት ተጠያቂነት</u>**

1) የቦርድ አባላት በዚህ ደንብ መሰረት የተሰጣቸውን ኃላፊነት ካለመወጣቸው የተነሳ በኢንተርፕራይዙ ላይ ለሚደርስ ጉዳት የግልና የጋራ ተጠያቂነት ይኖርባቸዋል፡፡
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ሥር የተደነገገው ቢኖርም፣ የቦርዱ ውሳኔ በሚሰጥበት ጊዜ ውሳኔውን በመቃወም በድምጽ የተለየ የቦርድ አባል ውሳኔው ከሚያስከትለው ተጠያቂነት ነጻ ይሆን ዘንድ አስተያየቱን በመጻፍ መፈረም አለበት፤
3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ሥር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ አንድ የቦርድ አባል በሚፈለገው ሁኔታ ሀላፊነቱን ካልተወጣ ቢሮው ወይም የቢሮው መዋቅር በማንኛውም ጊዜ በህጉ መሰረት የማስተካከያ እርምጃ ሊወስድበት ወይም ከአባልነት በማንሳት ሌላ ሰው ሊተካ ይችላል፡፡

**<u>ንዑስ ክፍል ሶስት</u>**

**<u>የስራ አስኪያጆች አስተዳደር ስርዓት (የምልመላ (የቅጥር) እና የምደባ ስርዓት)</u>**

**16.<u>የሥራ አስኪያጁ ቅጥር ወይም ምደባ እና ተጠሪነት</u>**

1) ቦርዱ ቢሮው የኢንተርፕራይዙን ስራ አስኪያጅ ለመቅጠር ወይም ለመመደብ በሚያወጣው መመሪያ በተገለጸው መሥፈርት መሰረት ለሥራው ውጤታማነት የሚያስፈልገውን ሰው መልምሎ በማወዳደር

qaxara woy gaama dandiitanno.

2) Konni quwi cinaancho quwa (1) worroonnihu noo gedeenni heerenna borde interpiraayizete qara loosu harisancho wolootu borro minanni woy interpiraayizubbanni dargu soorro assatenni gaantara dandiitanno.
3) Interpiraayizete loosu harisanchi qixire woy gamooshshi bordete gumulante ejensetenni kaajjitannoha ikkanno.
4) Loosu harisanchi hundaanchimma bordete ikkitanno.
5) Konni quwi tittirshu jeefishshi biddisunni gumulamanno.

**17. <u>Qaru Loosu Harisaaanchira Hundaancho Ikkitino Wolootu Loosu Sooreeye Qaxara, Gaamanna Deerru Lopho</u>**

1) Borde hundaanchimansa interpiraayizete qaru loosu harisaanchira ikkitino woloota bissa qaxara, gaama, deerru lophonna disipiliinete hunaanchimma lainohunni qaru loosu harisaanchinni shiqusero buuxxe kaajjishshanno.
2) Interpiraayizete qaru loosu harisaanchi bordete shiqishe gumulsiisatenni taalu deerrira no qaru loosu harisanchira hundaancho ikkitino loosu golla sooreeyye amanshiishannoha ikkino korkaatinni darga soorratenni gaamate dandaanno.

**18. <u>Loosu Ha’risaanchi Biilloonyenna Loosu Qeecha</u>**

Interpiraayizete loosu ha’’risaanchira aanino

መቅጠር ወይም መመደብ ይችላል፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ቦርዱ የኢንተርፕራይዙን ዋና ስራ አስኪያጅ ከሌሎች ጽ/ቤቶች ወይም ኢንተርፕራይዞች በማዛወር ሊመድብ ይችላል፡፡
3) የኢንተርፕራይዙ ስራ አስኪያጅ ቅጥር ወይም ምደባ በቦርዱ ተፈጽሞ በኤጀንሲው የሚፀድቅ ይሆናል፡፡
4) የስራ አስኪያጁ ተጠሪነት ለቦርዱ ይሆናል፡፡
5) የዚህ አንቀጽ ዝርዝር አተገባበር በመመሪያ ይወሰናል፡፡

**17.<u>ለዋና ስራ አስኪያጁ ተጠሪ የሆኑ ሌሎች የስራ ሀላፊዎች ቅጥር፣ ምደባ እና የደረጃ እድገት</u>**

1) ቦርዱ ተጠሪነታቸው ለኢንተርፕራይዙ ዋና ስራ አስኪያጅ የሆኑ ሌሎች አካላት ቅጥር፣ ምደባ፣ ደረጃ እድገት እና የዲሲፕሊን ቅጣት በዋና ስራ አስኪያጁ ሲቀርብለት መርምሮ ያጸድቃል፡፡
2) የኢንተርፕራይዙን ዋና ስራ አስኪያጅ ለቦርድ አቅርቦ በማስወሰን በተመሳሳይ ደረጃ ያለ ለዋና ስራ አስኪያጁ ተጠሪ የሆኑ የስረ ክፍል ሀላፊዎችን አሳማኝ በሆነ ምክንያት ቦታ በማለዋወጥ ሊመድብ ይችላል፡፡

**18.<u>የስራ አስኪያጁ ሥልጣንና ተግባር</u>**

የኢንተርፕራይዙ ሥራ አስኪያጅ የሚከተለው

biilloonyinna loosu qeechi heeʿʿrannosi:

1) Tenne wodho quwa 8 garinni interpiraayizete uyinoonni biilloonyenna loosu qeecha loosu aana hosiisanno;
2) Interpiraayizete loosu mixonna baajeete qixxeesanni boordete shiqishanno, fajjinirono loosu aana hosiisanno;
3) Interpiraayizete looso qineessanno; massaganno; gashshanno; illaallisanno;
4) Bordete uyinanni gumulonna raga jeefisanno jefisiisanno;
5) Interpiraayizete loosunna baajettete jeefishsha ripoorte yanna yannatenni qixxeessatenni bordete shiqishanno;
6) Borde affeenna interpiraayizete baankete shallago fananno, milli assanno, seeru garinni amadanno, interpiraayizete shallagonna jajji garunni amadamanno gede assanno;
7) Interpiraayizete loosaasine garimma noosi seerinni qaxaranno, gashshanno, loosunni geegisanno;
8) Loosoho hasiissanno babbaxitino haaro loosu harinshubba bordete shiqishe kajjishiishanno;
9) Sayikki bissa ledo assinanni xaadooshshe woy sumuumme lainohunni interpiraayize riqiwanno;
10) Gambooshshu ajandi balaxe bordete

ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል፡

1) በዚህ ደንብ አንቀጽ 8 መሰረት ለኢንተርፕራይዙ የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባራት ስራ ላይ ያውላል፤
2) የኢንተርፕራይዙን የስራና በጀት ዕቅድ በማዘጋጀት ለቦርድ ያቀርባል፤ ሲጸድቅም ስራ ላይ ያውላል፤
3) የኢንተርፕራይዙን ተግባር ያቀናጃል፤ ይመራል፤ ያስተዳድራል፤ ይቆጣጠራል፤
4) በቦርዱ የሚሰጠውን ውሳኔና አቅጣጫዎች ይፈጽማል፤ ያስፈጽማል፤
5) የኢንተርፕራይዙን የስራና በጀት አፈጻጸም ሪፖርት በየጊዜው በማዘጋጀት ለቦርድ ያቀርባል፤
6) በቦርዱ ዕውቅና የኢንተርፕራይዙን የባንክ ሒሳብ ይከፍታል፤ ያንቀሳቅሳል፤ በህጉ መሰረት ይይዛል፤ የኢንተርፕራይዙ ሒሣብና ንብረት በአግባቡ እንዲያዝ ያደርጋል፤
7) ሠራተኞች አግባብ ባለው ህግ ይቀጥራል፤ያስተዳድራል፤ ከሥራ ያሠናብታል፤
8) ለስራው የሚያስፈልጉ የተለያዩ አዳዲስ አሰራሮችን ለቦርዱ በማቅረብ ያስጸድቃል፤
9) ከሶስተኛ አካል ጋር የሚደረገውን ግንኙነት ወይም ስምምነት አስመልክቶ ኢንተርፕራይዙን ይወክላል፤
10) የስብሰባ አጀንዳ አስቀድሞ ለቦርድ አባላት

miillara iillanno gede assanno;

11) Interpiraayizete jironna woxi gorsu way owaante loosira calla hosasi kaajjado qorqorshanna harunso assanno;

12) Hasiisannoha ikke leelliro biilloonyesinna loosu qeechasi bocunni wolootu loosu massagaanonna loosaasinera riqiwotenni aanno;

13) Boordete woy ejensetenni uyinanni woloota loossa loossanno.

**19. <u>Loosu Harisaanchi Qoossonna Gadacho</u>**

1) Aye loosu harisaanchi uyinoonisi yawonna loosu qeechasi fultino poolise seerinna galtinote wodho garinninna ogimmate akatoome garinni loosa noosi.

2) Looosu harisaanchi horamishsha interpiraayizete giddooyidi galtinote wodhonni gumulantanno.

**20. <u>Loosu Harisaanchi Aana Gashshootame Qaafo Adha</u>**

1) Interpiraayize gumaame assate bordetenni adhinanni gumulo noo gedeenni heedhenna, interpiraayizete loosu harisanchi loosu jeefishshi woffi yiinoha ikkiro woy akkatoomete huno loosiro borde seeru garinni qaafo adhitara dandiitanno;

እንዲደርስ ያደርጋል፤

11)የኢንተርፕራይዙ ሀብትና ገንዘብ ለመስኖ ውሀ አገልግሎት ስራ ብቻ መዋሉን ጠንካራ ቁጥጥርና ክትትል ያደርጋል፤

12)አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከፊል ሥልጣንና ተግባሩን ለኢንተርፕራይዙ የስራ መሪዎችና ሰራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል፤እና

13)በቦርዱ ወይም በኤጀንሲው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ይፈጽማል፡፡

**19.<u>የሥራ አስኪያጆች መብቶች እና ግዴታዎች</u>**

1) ማንኛውም ሥራ አስኪያጅ የተሰጠውን ሀላፊነትእና ተግባሩን በወጡት ፖሊሲዎች፣ ህጎች እና መተዳደሪ ደንቦች መሠረት እና ሙያዊ ሥነ ምግባር በተላበሰ ሁኔታ ማከናወን አለበት፤

2) የሥራ አስኪያጁ ጥቅማ ጥቅሞች በኢንተርፕራይዙ የውስጥ መተዳደሪያ ደንብ ይወሰናል፡፡

**20.<u>በሥራ አስኪያጁ ላይ አስተዳደራዊ እርምጃ መውሰድ</u>**

1) ኢንተርፕራይዙን ውጤታማ ለማድረግ በቦርዱ የሚወሰደው ውሳኔ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የኢንተርፕራይዙ ሥራ አስኪያጅ የስራ አፈጻጸም ዝቅተኛ ከሆነ ወይም የስነ-ምግባር ጥፋቶችን ከፈጸመ ቦርዱ በህጉ መሰረት እርምጃ ሊወስድበት ይችላል፤

2) ቦርዱ በሥራ አስኪያጁ ላይ ከስራ የማሰናበት

2) Borde loosu harisaanchi aana loosu aaninni geegissate woy loosu harisanchimmanni kayisate qaafo adhitannoha ikkiro, gumulo loosu aana hossara dandiitannohu biirote woy biirote tantannora shiqqe kaajjituro ikkanno;
3) Konni quwi cinaancho quwa (1) garinni borde loosu harisaanchi aana loosu harisaanchimma biillonyinni kayisate qaafo adhitannoha ikkiro, interpirayizete giddo loosu deerrisi ledo haranno bayichi aana gaantannosi, hattoo base hooguro noo deerri aaana gaamamanno, jeefishshu fulanno biddisi aana gumulamanno.

**21. <u>Jawa Disipiliinete Qoricha A"dhisiisanno Huno</u>**

Tenne wodho quwa 20 garinni konni woroonni noo huno loosu harisaanchi aana jawa disipiliinete qaafo a"dhisiisanno:

1) Ejensete woy Ejensete tantano woy bordetenni uyinoonisi seeru borrote hajajo ayirisa hoogatenni woy afanni heere mootimmate loosu harinsho amurate woy poolise harunsa hoogatenni loosu aan agawajjo iillishatenni;
2) Interpiraayizete owatamaano afanni heere totayyeessa;
3) Loosu bayicho gibbo kakkayisatenni loosaasinete ledo giwama;
4) Dinbe woy jalli assitanno xagga horonsiratenni looso ea;
5) Muishsha adhatenni woy uuyinannisis gede xa"ma;
6) Awaaawurate woy ammano xeisate woy

ወይም ከስራ አስኪያጅነት የማንሳት እርምጃ የሚወስድበት ከሆነ፣ ውሳኔው ስራ ላይ ሊውል የሚችለው ለቢሮው ወይም ለቢሮው መዋቅር ቀርቦ ከጸደቀ ይሆናል፤

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት፣ ቦርዱ በሥራ አስኪያጁ ላይ ከስራ አስኪያጅነት ስልጣን የማንሳት እርምጃ የሚወስድበት ከሆነ፣ በኢንተርፕራይዙ ውስጥ የስራ ደረጃው በሚመጥንበት ቦታ ላይ ይመድበዋል፤ ተመጣጣኝ ደረጃ ከሌለ ባለው ደረጃ ላይ ይመድበዋል፤ አፈጻጸሙ በሚወጣው መመሪያ የሚወሰን ይሆናል።

**21.<u>ከባድ የዲሲፕሊን ቅጣት የሚያስከትሉ ጥፋቶች</u>**

በዚህ ደንብ አንቀጽ 20 መሰረት የሚከተሉት ጥፋቶች በስራ እስኪያጁ ላይ ከባድ የዲሲፕሊን እርምጃ ያስከትላሉ፤

1) በኤጀንሲው ወይም በኤጀንሲው የታችኛው መዋቅር ወይም በቦርድ የተሰጠውን ህጋዊ የጽሁፍ ትዕዛዝ ባለማክበር ወይም ሆን ብል የመንግስት አሰራር ሥርዓትን ወይም ፖሊሲን ባለመከተል በስራ ላይ ጉዳት ማድረስ፤

2) የኢንተርፕራይዙን ደንበኞች ሆን ብሎ ማመላለስ ወይም ማጉላላት፤

3) በስራ ቦታ ላይ ፀብ በማነሳሳት ከሰራተኞች ጋር መጣላት፤

4) በስካር ወይም የአደንዛዥ ዕፅን በመጠቀም ወደ ሥራ መግባት፤

5) እጅ መንሻ (ጉቦ) መቀበል ወይም እንዲሰጠው መጠየቅ፤

6) የማጭበርበር ወይም እምነት ማጉደል ወይም

kaphu loossa loosa;

7) Interpiraayizete jajja seerimale doogonni horonsira woy wolootu muishshu jaddo assotuwa loosa;
8) Interpiraayizete ledo horote kipho kalaqqara dandiitanno loossa loosa;
9) Biilloonye gariweelo horonsira;
10) Loosu bayicho koo/teemate aana coyinni qasa.

**22. <u>Loosu Harisaanchi Aana A՝՝dhinanni Gashshootame Qaafo Dana</u>**

Loosu harisaanchi akkatoomete huno hunino yine buunxiro a՝՝dhinanni jaddote xa՝՝mamooshshi noo gedeenni heerenna konni woroonni noo gashshootame qaafo a՝՝dhinara dandiinanni:

1) Loosu harisaanchimmanni kayisa;
2) Mittunni sasu agani geeshsha iillanno damoozu qoricha;
3) Loosu sheemata uurrisa woy loosunni geegissa.

**23. <u>Loosu Sheemata Urrisa</u>**

1) Loosu harisancho loosu sheemati konni woroonni noo korkaatubbanni uurrara dandaanno:
   (a) Interpiraayizetenna loosu harisaanchi suumumenni;
   (b) Loosu harisaanchi umisinni looso agurate hasiriro;
   (c) Loosu harisaanchi loosisi ledo xaadinohunni xisotenni xiwamironna

የማታለል ድርጊቶችን መፈጸም፤

7) የኢንተርፕራይዙን ንብረቶች በሕገ-ወጥ ምንገድ መጠቀም ወይም ሌሎች የሙስና ወንጀል ድርጊቶች መፈጸም፤
8) ከኢንተርፕራይዙ ጋር የጥቅም ግጭት ሊፈጥሩ የሚችሉ ድርጊቶችን መፈጸም፤
9) ስልጣንን አላግባብ መጠቀም፤
10) በሥራ ቦታ ያታዊ ትንኮሳ መፈጸም።

**22. <u>በሥራ አስኪያጁ ላይ የሚወሰዱ አስተዳደራዊ እርምጃ ዓይነት</u>**

ሥራ አስኪያጁ የስነምግባር ጥፋቶችን ፈጽሟል ተብሎ ከተረጋገጠ የሚወሰድበት የወንጀል ተጠያቂነት እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉት አስተዳደራዊ እርምጃዎች ሊወሰዱ ይችላል፤

1) ከሥራ አስኪያጅነት ማንሳት፤
2) ከአንድ እስከ ሶስት ወር የሚደርስ የደመወዝ መቀጮ፤
3) የሥራ ስምሪት ውል ማቋረጥ ወይም ከሥራ ማሰናበት።

**23.<u>የሥራ ውል ማቋረጥ</u>**

1) የሥራ አስኪያጁ የሥራ ውል በሚከተለት ምክንያቶች ሊቋረጥ ይችላል፤

(ሀ) በኢንተርፕራይዙ እና በሥራ አስኪያጁ ስምምነት መሠረት፤

(ለ) ሥራ አስኪያጁ በራሱ ተነሳሽነት ሥራውን ለመተው ከፈለገ፤

(ሐ) ሥራ አስኪያጁ ከሥራው ጋር በሚያያዝ በሽታ ከታመመ እና ሥራውን ማከናወን

loososi loosa hoogiro;

(d) Interpiraayize seerunni woy wolu korkaatinni goofimarchu geeshsha looso agurturo;

(e) Interpiraayizete loosi soorramate korkaatinni assinoonni tantanote soorro korkaatinni;

(f) Loosu gaamoshisi diigamiro woy karsamironna hakkuyi loosi loosu harisaancho wole basera dargu soorro assa dandiinanikkiha ikkiro;

(g) Loosu harisaanchi reyotenni baxxiro;

(h) Loosu harisaanchi loosu yannasi gude xurata fuliro;

(i) Loosu harisaanchi gaamamino looso loosate hasiissanosi ogimma hooge leellironna qajeelsha uyineenasino umosi loossa hoogasinni wole basera darigu soorro assine loosisa dandiinanikkiha ikkiro;

(j) Tenne wodhoninna fultano loosu harisaano galtinote wodho garinni loosunni geegisasira dandaanno jawa disipiliinete huno loose leelliro;

(k) Loosu harisaanchi gumulantino yannara qaxaraminoha ikkironna sheematu yanna goofuro;

(l) Loosu aana iillitinosi hegeraawe woy yannate geeshshi loosu gawajjonni kainohunni looso loosate dandaa hoogironna tinino xagishshu tajenni buuxanturo;

ካልቻለ፤

(መ) ኢንተርፕራይዙ በህግ ወይም በሌላ ምክንያት በቋሚነት ሥራውን ካቆመ፤

(ሠ) የኢንተርፕራይዙ ተግባር በመለወጡ ምክንያት በተደረገው የመዋቅር ለውጥ የተነሣ፤

(ረ) የሥራ መደቡ ሲፈርስ ወይም አንድ ላይ ሲመጣ (ሲቀላቀል) እና የዚያን ተግባር ሥራ አስኪያጅ ወደ ሌላ ማዛወር የማይቻል ከሆነ፤

(ሰ) ሥራ አስኪያጁ በሚሞትበት ጊዜ፤

(ሸ) ሥራ አስኪያጁ ጡረታ ከወጣ፤

(ቀ) ሥራ አስኪያጁ የተመደበበትን ሥራ ለመስራት የሚያስፈልገውን ችሎታ አጥቶ ከተገኘ እና ሥልጠና ቢሰጠውም እራሱን ማብቃት ባለመቻሉ ወደ ሌላ አዛውሮ ማሰራት ካልተቻለ፤

(በ) በዚህ ደንብ እና በሚወጣው የሥራ አስኪያጆች መተዳደሪያ ደንብ መሰረት ከስራ ሊያሰናብተው የሚችል ከባድ የዲሲፒሊን ጥፋት ፈጽሞ ከተገኘ፤

(ተ) ሥራ አስኪጁ ለተወሰነ ጊዜ የተቀጠረ ከሆነ እና የውሉ ጊዜ ከተጠናቀቀ፤

(ቸ) በስራ ላይ በደረሰበት ቋሚ ወይም ጊዜያዊ የሥራ ጉዳት የተነሣ ሥራ መስራት ካልቻለና ይሄውም በህክምና ማስረጃ ከተረጋገጠ፤

(m) Loosu harisaanchi 15nna hakuyi aleenni harunsino loosu barra ikkadiweelo korkaatinni loosunni gatinoha ikkironna tonnu barri giddo egensiishshunni woshshineenna loosunni gatino barrira ikkado taje shiqisha hoogiro;

(n) Jaddote qaxxarame 3 aganininna hakuyi aleenni qorichamiro.

2) Loosu harisaanchi konni quwinni cinaanchu quwi (1) (b) garinni loososi agurate hasiriro 30 barri albaanni bordete borrotenni egensiisa noosi.

3) Loosu harisaanchi konni quwinni cinaancho quwi (2) garinni bordete borrotenni egensiisa hoogiro garimma noosi seerinni xa'ʼmamanno.

**24. <u>Gashshootame Qaafo A'ʼdhinanni Amanyoote</u>**

1) Borde akkatoomete huno loosu harisaanchi loosino yitanno ku'ʼlaato iilitusero boredete miilla mereerinni 3 miilla noose akkatoomete komite urrisatenni disipiliinete buuxo assite gumulote hedo shiqishshanose gede assitanno.

2) Borde loosu harisanchi aana disipiliinete qaafo a'ʼdhituro gumulo borrotenni qixxeessite loosu harisaanchira ontu loosu barri giddo uuyitanno.

3) Loosu harisaanchi konni quwinni cinaancho quwi (2) garinni iillitinosi bordete gumulo aana koffeenyu heerisiro gumulo iillitusi barrinni hanafe noo 30 barri giddo koffeenyasi biirote woy hundaancho ikkitino biirote tantanora shiqisha noosi.

4) Biiro woy biirote tantano konni quwi

(ነ) ሥራ አስኪጁ ለ15 እና ከዚያ በላይ ተከታታይ የስራ ቀናት ያለበቂ ምክንያት ከስራ የቀረ እንደሆነ እና በአስር ቀናት ውስጥ በማስታወቂያ ተጠርቶ ከሥራ ቀናት ለቀረባቸው በተጨባጭ ማስረጃ ካላቀረበ፤

(ኘ) በወንጀል ከተከሰሶ ለ3 ወር እና ከዚያ በላይ ከተፈረደበት፡፡

2) ሥራ አስኪጁ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (ለ) መሠረት ሥራውን ለመልቀቅ ሲፈልግ ከ30 ቀናት በፊት ለቦረዱ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

3) ሥራ አስኪጁ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ለቦረዱ በጽሁፍ ካላሳወቀ አግባብ ባለው ህግ ይጠየቃል፡፡

**24. <u>የአስተዳደራዊ እርምጃ አወሳሰድ ሥነ-ስርዓት</u>**

1) ቦርዱ የሥነ ምግባር ጥፋት በሥራ አስኪያጁ ሥለመፈጸሙ ጥቆማ ሲደርሰው ከቦርድ አባላት መካከል 3 አባላት ያለው የሥነ-ምግባር ኮሚቴ በመመስረት የዲሲፕሊን ምርመራ ተካሂድ የውሳኔ ሃሳብ እንዲያቀርብለት ሊያደርግ ይችላል፡፡

2) ቦርዱ በሥራ አስኪያጁ ላይ የዲሲፕሊን እርምጃ ሲወስድ ውሳኔውን በጽሑፍ አዘጋጅቶ ለሥራ አስኪያጁ በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ይሰጣል፡፡

3) ሥራ አስኪያጁ በዚህ እንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት በደረሰው የቦርድ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ካለው ውሳኔው ከደረሰው ቀን ጀምሮ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለቢሮው ማቅረብ አለበት፡፡

4) ቢሮው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3)

cinaancho quwi (3) garinni koffeenyu iillisero gumulo iilituse barrinni hanafe noo 30 barri giddo hajo buuxe uuyinoonni gumulo kaajjishate woy shaaratenni gumulte gumulo borrotenni loosu harisaanchiranna bordete egensiisa noose.

5) Biiro woy biirote tantano loosu harisaanchinni shiqino koffeennya buuxxe goofimarchu gumulo uyita geeshsha bordete gumulo kiante keeshshitanno gede assitara dandiitanno.

6) Biiro woy biirote tantano uuyitino gumulo aana koffeenyu noosi loosu harisaanchi gumulo iillitusi barrinni hanafe lamu again giddo koffeenya ha"nuura yoo minira shiqisha dandaanno.

## GAFA SASE

## GORSU WAY OWAANTE MAAMARA

## CINAANCHO GAFA MITE

## GORSU WAY HORAAMEYYE MAAMARI UURRA, TANTANO, HUNDAANCHIMMA, BIILLOONYENNA LOOSU QEECHA

**25. Horaameeyyete Maamari Uurranna Miilla**

1) Gorsu way horaameeyye maamarra hasatto noonsa manootinni fajjaalesimatenni woy tenne wodho garinni gorsu way sufaminoha, farconnihanna gumaame ikkitino doogonni horonsiratenna gashshate dandiinanni gede qorqoranno bisinni uurrara dandaanno.

2) Maamaru seeru mannimma afi'ra dandaannohu Ejensetenni borreessamiro callati.

መሠረት ቅሬታው ሲደርሰው ውሳኔው ከደረሰው ቀን ጀምሮ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ ጉዳዩን መርምሮ የተሰጠውን ውሳኔ በማጽናት ወይም ውድቅ በማድረግ ወስኖ ውሳኔውን በጽሁፍ ለሥራ አስኪያጁና ለቦርዱ ማሣወቅ አለበት፡፡

5) ቢሮው ሥራ አስኪያጁ ያቀረበውን ቅሬታ መርምሮ የመጨረሻ ውሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ የቦርዱ ውሳኔ ታግዶ እንዲቆይ ማድረግ ይችላል፡፡

6) ቢሮው በሰጠው ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ሥራ አስኪያጅ ውሳኔው ከደረሰው ቀን ጀምሮ በሁለት ወር ውስጥ ቅሬታውን ለመደበኛ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል፡፡

## ክፍል ሶስት

## የመስኖ ውሃ አገልግሎት ማህበር

## ንዑስ ክፍል አንድ

## የመስኖ ዉሃ ተጠቃሚዎች ማህበር መቋቋም፤ አደረጃጀት፤ ተጠሪነት፤ ሥልጣንና ተግባር

2) Maamaru gorsu way horonsiraano maamarra taje aaninni rigidami barrinni hanafe diigaminohu gede kiirranni.

**54. Maamara Interpiraayizete Widira Lossa**

1) Tenne wodho quwa 6 worroonni safaraano garinni gorsu way owaante horonsiraano maamari interepiraayizete widira lophara



በመረከብ ጉዳት እንዳይደርስባቸው ያደርጋል፤

(ለ) የማኅበሩን ሀብትና ንብረት ይሰበስባል፤

(ሐ) ከማኅበሩ ገንዘብ ጠያቂ የሆኑ ሰዎችን ይጠራል፤

(መ) የማኅበሩ ጠቅላላ ጉባኤ በወሰነው እና በኤጀንሲው በፀደቀው ውሳኔ መሠረት የማኅበሩን ሀብትና ንብረት ያከፋፍላል፤

(ሠ) የሂሳብ ማጣራቱን ሥራ በሚገባ ለማከናወን በሚያስፈልግ መጠን የማኅበሩን ሥራ ያንቀሳቅሳል፤

(ረ) ማኅበሩን የሚመለከቱ ክርክሮችን ያካሂዳል፡፡

3) የማኅበሩ የመፍረስ ሂደት እስከሚጠናቀቅ ድረስ የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች፣ የማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ በማኅበሩና በአባላቱ ላይ ተፈፃሚ መሆናቸው ይቀጥላል፤

4) የሂሳብ አጣሪው የአገልግሎት ዋጋ ከማኅበሩ ሂሳብ የሚከፈል ይሆናል፡፡

**53.ማኅበርን ከመዝገብ ስለመሰረዝ**

1) የሂሳብ ማጣራቱ ስራ እንደተጠናቀቀ ኤጀንሲው ማኅበሩን ከመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ማኅበራት መዝገብ ይሰርዛል፤

2) ማኅበሩ ከመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ማኅበራት መዝገብ ከተሰረዘበት ቀን ጀምሮ እንደፈረሰ ይቆጠራል፡፡

**54.ከማህበር ወደ ኢንተርፕይዝ ማሳደግ**

1) በዚህ ደንብ አንቀፅ 6 በተደነገገው መስፈርት መሰረት የመስኖ ዉሃ አገልግሎት ተጠቃሚዎች ማህበር ወደ ኢንተርፕራይዝ

dandaanno.

2) Horonsiraanote maamari Konni quwi cinaancho quwa (1) la’noonni safaraano wonshannoha ikkiro, Ejense maamara interpiraayizete widira loossate gumultano.

3) Ejense Konni quwi cinanco quwa (1) nna (2) la’’noonniha kaima assidhe maamara interepiraayzete widirea loossate gumulturo interpiraayizete su’’ma, seeru mannima afamooshu woraqatanna uynoonni barra leellishano sanade aa noose.

4) Konni quwi cinaancho quwa (3) garinni mittu maamari interpiraayizete widira lophiro su’’ma “Gorsu Way Owaante Interpiraayize“yine borreessine seeru mannima afamooshu woraqata uynanni.

## GAFA SHOOLE

## EJENSETE, ZOONETENNA WORADU GASHSHOOTI BIILLOONYENNA LOOSU QEECHA

**55. Ejensete Biilloonyenna Loosu Qeecha**

Wolootu seerubbanni uynoonni biilloonyinna loosu qeechi noo gedeenni hee‘’reenna Ejensete tenne wodho jeefisate konni woroonni noo biilloonyinna loosu qeechi hee‘’rannose:

1) Interpiraayize woy maamaru aanno gorsu way owaante gobbate poolise, istiraatejenna seerubba garininna qoqqowu dagoomi

ያድጋል።

2) የተጠቃሚዎች ማኅበር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተውን መስፈርት የሚያሟላ ከሆነ፣ ኤጀንሲው ማህበሩን ወደ ኢንተርፕራይዝ ለማሳደግ ይወስናል።

3) ኤጀንሲው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) የተመለከተውን መሠረት አድርጎ ማህበሩን ወደ ኢንተርፕራይዝ ለማሳደግ ሲወስን የኢንተርፕራይዙን ስም፣ ሕጋው ሰውነት የምስክር ወረቀት እና የተሰጠበትን ቀን የሚያሳይ ሰነድ መስጠት አለበት።

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት አንድ ማህበር ወደ ኢንተርፕራይዝ ካደገ ስሙ ‘የመስኖ ውሃ አገልግሎት ኢንተርፕራይዝ’ ተብሎ ተመዝግቦ የሕጋዊ ሰውነት የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል።

## ክፍል አራት

## የኤጀንሲው፣ የዞን እና የወረዳ አስተዳደር ሥልጣንና ተግባር

**55.የኤጀንሲው ሥልጣንና ተግባር**

በሌሎች ህጎች የተሰጠው ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ኤጀንሲው ይህን ደንብ ለማስፈጸም የሚከተለው ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል፤

1) ኢንተርፕራይዙ ወይም ማህበሩ የሚሰጠው የመስኖ ውሃ አገልግሎት በሀገሪቱ ፖሊሲ፣ ስትራተጂና ህጎች መሰረት እና በክልሉ ህብረተሰብ ባህልና ወግ ላይ የተመሰረተ

woganna budu aana xintaminoha ikkasi ha‟runsitanno, qorqortanno;

2) Interpiraayize woy maamaru gorsu way owaante uyinanni gara yannitenna duushshitanno garinni jeefisate dandiitanno gede hasiisanno irkonna kaa‟lo baala assitanno;
3) gorsu way owaante uyitanno interpiraayize woy maamarra loosonsa ikkadimmate loossanno gede loosu jeefishshi biddissa, loosu manuwaalenna istaandarde qixxeessitanno, qorqortanno, loosu aana hosase ha‟runsitanno;
4) Jajjunna woxu irko mootimmatenna mootimmannita ikkitinokki bissanni kaa‟lotenni, liqoo aate garinni afi‟nanni gara injeesitanno;
5) Interpirayizubanniti woy maamarranniti tekinikete wolqa ijarantanno gede yannate ledo ha‟ranno gara injeesitanno, irkissanno, harunsitanno;
6) Interpiraayizubbate woy maamarrate jajja horonsi‟nanni gara, woxu amadooshe yanna yannate qorqoramanno gede assitanno, harunsitanno, hasiissanno irko uytanno;
7) Gorsu way owaante shiqo wolqa ijaarrate loossa loossanno, tekiniketenna amaalete irko uytanno;
8) Interipiraayizubba woy mammarrate wolqa aleenni ikkitino haaro gorsu way owaante shiqo xiinxawonna diizayine, woyyeessatenna halashshate loossa hasiishshu garinni jeefisanno, jefisiissanno;
9) Mootimmate baajetenni woy liqootenna

መሆኑን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

2) ኢንተርፕራይዝ ወይም ማህበር የመስኖ ውሃ አገልግሎት አሰጣጥን በዘመናዊና አጥጋቢ በሆነ መልኩ ለመፈጸም እንዲችሉ አስፈላጊውን ድጋፍና እርዳታ ሁሉ ያደርጋል፤
3) የመስኖ ውሃ አገልግሎት ሰጪ ኢንተርፕራይዝ ወይም ማህበር ተግባራቸውን በብቃት እንዲያከናውኑ የስራ አፈጻጸም መመሪያ፣ የስራ ማኑዋልና ስታንዳርድ ያዘጋጃል፤ ይቆጣጠራል፤ ሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፤
4) የንብረትና የገንዘብ ድጋፍ ከመንግስትና መንግስታዊ ካልሆኑ አካላት በዕርዳታ፣ በብድርና በስጦታ መልክ የሚገኝበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤
5) ኢንተርፕራይዙ ወይም ማህበሩ የቴክኒክ አቅም እንዲገነባና ከወቅቱ ጋር እንዲራመድ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤ ይደግፋል፤ይከታተላል፤
6) የኢንተርፕራይዙ ወይም የማህበሩ የንብረት አጠቃቀምና የገንዘብ አያያዝ በየጊዜው እንዲመረመር ያደርጋል፤ይከታተላል፤ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፤
7) የመስኖ ውሃ አገልግሎት አቅርቦት አቅም ግንባታ ስራዎችን ያካሂዳል፤ የቴክኒክና የምክር ድጋፍ ይሰጣል፤
8) ከኢንተርፕራይዙ ወይም ከማህበሩ አቅም በላይ የሆኑ አዳዲስ የመስኖ ውሃ አገልግሎት አቅርቦት የምርምርና ዲዛይን፣ የማሻሻል እና የማስፋፋት ስራዎችን እንደ አስፈላጊነታቸው ይፈጽማል፤ ያስፈጽማል፤
9) በመንግስት በጀት ወይም በብድርና በሌሎች

woolootu bissa irkonni harinsanni gorsu way ijaaru projekitubbate loossa harunsitanno, qorqoratnno, hasiisanno irko uuyitanno;

10) Interpirayizubba invetimentete fulo qola woy diwa dandiisisanno gara dirunni codhinanni shallago giddo codhitannore ikkansa harunsitanno, qorqortanno;

11) Xiinxalline shiqinshoonisi gorsu way interpirayizubbanna maamarra tantanonna taarife Biirote widoonni kaajjitanno gede asiissanno;

12) Hundanchimansanni gumulamikkinni interpiraayizete woy maamaru loosu jeefishsha gafa gansiisate hasiissanno loosu irkonna harunso assitanno;

13) Interpirayizubbate woy maamarrate aana yanna agarino loosu keeno, qortonna hiise assitanno, loosu xe''ne noo baserano taashshote qaafo adhitanno, adhinanni gede assitanno.

**56. <u>Zoonetenna Woradu Gashshooti Biillonyenna Loosu Qeecha</u>**

1) Interpiraayibuatenna maamarrate hasiissanno irko aanno;
2) Seeru garinni borrote mine ijaarsinanni woy babbaxino ijaarira woy gorsu way looso ijaarate bayicho interpiraayizete woy maamaraho injeessanno;
3) Interpiraayizete woy maamaru wolqa aleenni ikkitino haaro gorsu way doogo diriirsate loossa woy gorsu way ijaari ledo xaaddino loossa woy gatamarshshunna soorrote udiine loosate baajete gaamatenni

አካላት ድጋፍ የሚካሄዱ የመስኖ ውሃ ግንባታ ፕሮጀክቶች ስራዎችን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፤

10) ኢንተርፕራይዞች የኢንቨስትመንት ወጪን መመለስ ወይም መተካት በሚያስችል ሁኔታ በዓመት በቁጠባ ሂሳብ ውስጥ የሚያስቀምጡ መሆናቸውን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

11) ተጠንቶ የቀረበለትን የመስኖ ውሃ ኢንተርፕራይዞችና ማህበራት መዋቅርና ታሪፍ በቢሮ በኩል እንዲፀድቅ ያስደርጋል፤

12) በተጠሪነቱ ሳይወሰን የኢንተርፕራይዝ ወይም የማህበር የስራ አፈጻጸምን ለማሳካት አስፈላጊውን የስራ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፤

13) ለኢንተርፕራይዝ ወይም ለማህበር ጊዜውን የጠበቀ የስራ ግምገማ፣ ምዘና እና ሂስ ያደርጋል፤ የስራ ጉድለት ባለበት ቦታም የማስተካከያ እርምጃ የወስዳል፣ እንዲወሰድ ያደርጋል።

**56. <u>የዞን እና የወረዳ አስተዳደር ሥልጣንና ተግባር</u>**

1) ለኢንተርፕራይዝ፣ለማህበር አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፤
2) በህጉ መሰረት የጽህፈት ቤት መገንቢያ ወይም ለተለያዩ ግንባታዎች ወይም የመስኖ ውሃ ስራ መገንቢያ ቦታ ለኢንተርፕራይዝ፣ለማህበር ያመቻቻል፤
3) ከኢንተርፕራይዝ ወይም ከማህበር አቅም በላይ ለሆኑ ለማካሄዱ አዳዲስ የመስኖ ውሃ መስመር መዘርጋት ስራዎች ወይም ከመስኖ ውሃ ግንባታ ጋር የተያያዙ ስራዎች ወይም የጥገና እና የመለዋወጫ ዕቃዎች ስራዎችን

loosiisanno;

4) Interpirayizubba woy maamarra gorsu way pirojektubba ijaarshu looso loosamannokki gede guficho ikkitino hajubba annimatenni tiranno.

**57. <u>Interpiraayizubbanna Maamarra Qarqaru Gashshoti Bisi Ledo Heeranonsa Xaadoshshe</u>**

1) Tenne wodhonni worroonni wole woro noo gedeenni heedhenna woradunna olluu gashshooti tantano biillonyinsa qoqqowi giddo afantanno interpirayizubbanna maamarra loosu harinsho wolaphonsa ayirisatenni loosu millimilonsara garimma noose irko aa noonsa.

2) Mitte interpiraayize woy maamari owaantete qoqqowi way kalaqamunni daadanno gara harunsatenni mitte zoonenni, worada woy olluu gashshooti danna balaxosi garinni wolu zoone, woradi woy olluu gashshooti danna sa’annoha ikkiro mittu mittunkku gashshootu bisinni riqiwantanno miilla noose komite interpiraayizete woy maamaru hajo lainohunni gashshootu tantano ledo xaadisannore ikkite loossanno.

## GAFA ONTE

## TAARIFE, DOOGO DIRIIRSANNA KARSIISA

**58. <u>Onwaantete Baatooshshi Jeefishsha</u>**

1) Aye interpiraayize woy maamari fulo diwate miilu owaantete qoqqowi giddo amadino baattote hala’linye woy latisanno laalchi dana woy horonsiranno gorsu way

በጀት በመመደብ ያሰራል፤

4) የኢንተርፕራይዝ፣ማህበር መስኖ ውሃ ፕሮጀክቶች ግንባታ ስራ እንዳይሰራ እንቅፋት የሆኑ ጉዳዮችን በባለቤትነት ይፈታል።

**57.<u>ኢንተርፕራይዞች እና ማህበራት ከአካባቢ አስተዳደር አካል ጋር ስለሚኖራቸው ግንኙነት</u>**

1) በዚህ ደንብ የተደነገጉ ሌሎች ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የወረዳና የቀበሌ መስተዳድር መዋቅሮች በሥልጣን ክልላቸው ውስጥ ለሚገኙ ኢንተርፕራይዞች እና ማህበራት የአሠራር ነፃነታቸውን በማክበር ለሥራ እንቅስቃሴአቸው ተገቢነት ያለው ድጋፍ መስጠት አለባቸው።

2) የአንድ ኢንተርፕራይዝ ወይም ማህበር የአገልግሎት ክልል የውሃውን የተፈጥሮ አወራረድ ተከትሎ ከአንድ ዞን፣ ወረዳ ወይም ቀበሌ አስተዳደር ወሰን እንደ ቅደም ተከተሉ ወደ ሌላው ዞን፣ ወረዳ ወይም ቀበሌ አስተዳደር ወሰን የሚሻገር ከሆነ ከእያንዳንዱ አስተዳደር አካል የሚወከሉ አባላት ያሉበት ኮሚቴ የኢንተርፕራይዙ ወይም የማህበሩን ጉዳይ በተመለከተ ከአስተዳደር መዋቅሩ ጋር አገናኝ ሆነው ይሰራሉ።

## <u>ክፍል አምስት</u>

## <u>ታሪፍ፣መስመር መዘርጋት እና መዋሀድ</u>

**58.<u>የአገልግሎት ክፍያ አፈጻጸም</u>**

1) ማንኛውም ኢንተርፕራይዝ ወይም ማኅበር ወጪዎችን ለመሸፈን አባሉ በአገልግሎት ክልል ውስጥ የያዘውን የማሳ ስፋት ወይም የሚያመርተውን የሰብል ዓይነት ወይም

bikka kaima assino diru gataamarshunna looso harinsanni baatooshshe baatisiisa noosi;

2) Koni quwi cinaancho quwa (1) garinni mittu mittunku miili baatanno gataamarshunna looso harinsanni baatooshshi:

(a) Gorsunna du'namaanchu awutaare looso harisate, gatamarsatenna way sa'ano aye bohe coicha assate hasiissanno fulo diwate;

(b) Gorsunna du'namaanchu awutaare looso harisate woy way sa'anno doogo fanate owaantera uyinanni woloota owaante uyitanorira baantanni baatooshshe diwate;

(c) Interpiraayitenna maamaru loosaasine damoozanna wole fulo diwate; nna

(d) Interpiraayizetenna maamaraho agarooshshu yanna woxe suuqate hosannoha ikkanno.

3) Mitte interpiraayize woy maamari mittu mittunku miili gorsu loosisira horonsiranno way bikka woy latisanno gorsu baatto bikki aana xintamino owaantete baatooshshe baatanno gede assa dandaanno. Tittirshu jeefishshi tenne wodho jeefisate fulanno biddisinni gumulamanno.

4) Shiima woxu fulo noose interpiraayize woy maamari miilla sumuumetenni diro miillate fushsho bocunni wolqate ka'loninna danunni ikkanno gede assa

የሚጠቀመውን የመስኖ ውሀ መጠን መሠረት ያደረገ ዓመታዊ የጥገና እና የሥራ ማስኬጃ ክፍያ ማስከፈል አለበት፤

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት እያንዳንዱ አባል የሚከፍለው የጥገና እና የሥራ ማስኬጃ ክፍያ፤

(ሀ) የመስኖና ድሬኔጅ አውታሩን ለማካሄድ፣ ለመጠገንና የውሃ መተላለፍያ ማንኛውም ቦይ ለማጽዳት የሚያስፈልገውን ወጪ ለመሸፈን፤

(ለ) የመስኖና ድሬኔጅ አውታሩን ሥራ የማካሄድ ወይም የውሃውን መተላለፍያ መንገድ የመክፈት አገልግሎት ለሚሰጡ ሌሎች አገልግሎት ሰጭዎች የሚደረጉ ክፍያዎችን ለመሸፈን፤

(ሐ) የኢንተርፕራይዙን ወይም የማኅበሩን ሠራተኞች ደመወዝ እና ሌሎች ወጪዎች ለመሸፈን፤ እና

(መ) ኢንተርፕራይዙ ወይም ለማኅበሩ የመጠባበቂያ ገንዘብ ተቀማጭ ለማድረግ የሚውል ይሆናል፡፡

3) አንድ ኢንተርፕራይዝ ወይም ማኅበር እያንዳንዱ አባል ለመስኖ እርሻው በሚጠቀመው የውሃ መጠን ወይም በሚያለማው መስኖ መሬት መጠን ላይ የተመሰረተ የአገልግሎት ክፍያ እንዲፈጽም ማድረግ ይችላል፡፡ ዝርዝር አፈፃፀሙ ይህንን ደንብ ለማስፈፀም በሚወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

4) አነስተኛ የገንዘብ ወጪ ያለበት ኢንተርፕራይዝ ወይም ማኅበር አባላት በስምምነት ዓመታዊ የአባላት መዋጮው ከፊል የጉልበት አስተዋጽኦን ጨምሮ

dandiitanno.

5) Konni quwira cinaancho quwa (1) kayise (3) geeshsha worroonnihu noo gedeenni heerenna, bikkamino manni baatooshiweelo gorsu way owaante afidhara dandiitanno gara fulanno biddisinni gumulara dandiinanni.
6) Gorsu way owaantete taarifete bikki xiinxallo kaima assatenni interpiraayizete borde woy maamaru xaphoomu songonni gumulamannoha ikkanno.

**59. <u>Investmentete Fulo Qolate Miillatenni Gamba Assinanni Baatooshshe Lainohunni</u>**

Interpiraayize woy maamaru yannite gorsu du'namaanchi owaante ijaarira fultino investmentete fulo miillate baatate wolqa hedote giddo worino garinni horonsidhanno waa woy latisanno gorsu baatto bikka kaima assite gama baatooshshe gamba assatenni hajo la'anno bisira higano gede assitanno. Tittirshu jeefishshi tenne wodho jeefisate fulanno biddisinni xawinsanni.

**60. <u>Interpiraayize woy Maamara Karsiisa</u>**

1) Ejense dagate owaante uynanni gara ledatenna danchu gahshshooti qarra tirate dandiisiissanno yite ammanturo, xiinxallo kaima assatenni lamenna hakkunni aleenni ikkitino interpiraaayizubba woy horaameeyyete maamarra karsiisantanno gede gumultara dandiitanno.
2) Interpiraayize woy horaameyye maamarra karsiisantanno yannara qoosonsanna

በዓይነት እንዲሆን ማድረግ ይችላል፡፡

5) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እስከ (3) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የተወሰኑ ሰዎች ያለክፍያ የመስኖ ውሃ አገልግሎት ሊያገኙ የሚችሉበት ሁኔታ በሚወጣው መመሪያ ሊወሰን ይችላል፤

6) የመስኖ ውሃ አገልግሎት ታሪፍ መጠን በጥናት ላይ ተመስርቶ የኢንተረፕራይዙ ቦረድ ወይም በማህበሩ ጠቅላላ ጉባዔ የሚወሰን ይሆናል፡፡

**59.<u>የኢንቨስትመንት ወጪን ለመመለስ ከአባላት ስለሚሰበሰብ ክፍያ</u>**

ኢንተርፕራይዙ ወይም ማህበሩ ለዘመናዊ መስኖ ድሬኔጅ ግንባታ የወጣውን የኢንቨስትመንት ወጪ የአባላቱን የመክፈል አቅም ባገናዘበ ሁኔታ የሚጠቀሙትን ውሃ ወይም የሚያለሙትን የመስኖ መሬት መጠን መሰረት አድርጎ የተወሰነውን ክፍያ በመሰብሰብ ጉዳዩ ለሚመለከተው አካል እንዲመለስ ያደርጋል፡፡ ዝርዝር አፈፃፀሙ ይህንን ደንብ ለማስፈፀም በሚወጣው መመሪያ ይገለፃል፡፡

**60.<u>ኢንተርፕራይዝ ወይም ማህበርን ማዋሀድ</u>**

1) ኤጀንሲው የህዝብ አገልግሎት አሰጣጥን ለመጨመር እና የመልካም አስተዳደር ችግርን ለመፍታት ያስችላል ብሎ ካመነበት፣ በጥናት ላይ በመመስረት ሁለት እና ከዚያ በላይ የሆኑ ኢንተርፕራይዝ ወይም የተጠቃሚዎች ማህበራት እንዲዋሀዱ ሊወስን ይችላል::

2) ኢንተርፕራይዞች ወይም የተጠቃሚዎች ማህበራት በሚዋሀዱበት ጊዜ፣መብትና

gadachonsa haaro kalaqantino interpiraayize woy horaameeyyete maamarrara saynsanniha ikkanno.

3) Interpiraayize woy horaameeyyete maamarra karsiisantanno yannara mitto su"ma su"misanno su"minsoonni su"manno Ejense buuxxanno qoleno maareekitanno.
4) Konni quwi garinni karsiisantino uurrinsha woy horaameeyyete maamari gashshooti amuraati fulanno biddisinni gumulamannoha ikkanno.

**61. Interpiraayizete woy Maamaru Diigama**

Mitte interpiraayize woy maamari babbaxino korkaatinni diigamannoha ikkiro jajjisi tenne wodho garinni mootimmate jajja ikkanno.

**GAFA LEE**

**GORSU WAY AFAMANNO BUICHO AGAROOSHSHI, TUWAANYONNA JIRO AGARSIISA**

**62. Gorsu Way Doogo Agarooshshe**

1) Hiikuno gorsu way doogo loosi hasiisanno agarooshshe assa hasiissanno, tittirshu jeefishshi biddisunnu gumulamanno.
2) Aye manchi minisi qarqarira gorsu way seerimale doogonni du'namanokki gede agarooshshe assa noosi, way du'namanni noota afanno yannara interpiraayizete woy maamaraho egensiisa noosi.

ግዴታዎቻቸው አዲስ ወደ ተፈጠረው ኢንተርፕራይዝ ወይም የተጠቃሚዎች ማህበር የሚተላለፍ ይሆናል::

3) ኢንተርፕራይዞች ወይም የተጠቃሚዎች ማህበራት በሚዋሀዱበት ጊዜ አንድ ስም ይሰይማሉ የተሰየመውን ስም ኤጀንሲው ያረጋግጣል፤ ይመዘግባል::
4) በዚህ አንቀጽ መሰረት የተዋሐደው ኢንተርፕራይዝ ወይም የተጠቃሚዎች ማህበር አስተዳደር ሥርዓት በሚወጣው መመሪያ የሚወሰን ይሆናል፡፡

**61.የኢንተርፕራይዝ ወይም ማህበር መፍረስ**

አንድ ኢንተርፕራይዝ ወይም ማህበር በተለያዩ ምክንያቶች የሚፈርስ ከሆነ፣ ንብረቱ በዚህ ደንብ መሰረት የመንግስት ንብረት ይሆናል፡፡

**ክፍል ስድስት**

**የመስኖ ውሃ ምንጭ ጥበቃና እንክብካቤ እና ሀብቱን ማስከበር**

**62.የመስኖ ውሃ መስመር ጥበቃ**

1) ማንኛውም የመስኖ ውሃ መስመር ስራ አስፈላጊው ጥበቃ ሊደረግለት ይገባል፤ የአፈጻጸም ዝርዝሩ በሚወጣው መመሪያ የሚወሰን ይሆናል፡፡
2) ማንኛውም ሰው በቤቱ አካባቢ የመስኖ ውሃ በህገወጥ መንገድ እንዳይፈስ ጥበቃ ማድረግ አለበት፤ ውሃ እየፈሰሰ መሆኑን በሚያይበት ጊዜ ለኢንተርፕራይዙ ወይም ለማህበሩ ማሳወቅ አለበት፡፡

**63. Gorsu Way Afamano Bayichonna Qarqara Gashshanna Tuwata**

Aye gorsu way interpiraayize woy maamarira aantino qoossonna yawo heedhanosi:

1) Gorsu way buicho afantanno baycho gashsha, towatanna garunni amada hattono way buicho lophora kaaʻʻlitanno kaashuwa way buicho qarqarira kaasa;
2) Hajo laʻʻannosi bisi ledo ikkatenni gorsu way afamanno baycho qoqqowe amada;
3) Qoqqomboonni way afamanno qraqarira waa mooshshitanno kaashshuwa kaansannikki gede hoola;
4) Qoqqomboonni gorsu way afamanno qarqarira kaashshuwa huna, muranna addi addi ijaarruwa harinsanikki gede hoola noose.

**64. Gorsu Way Interpiraayize woy Maamari Amadooshshe Agarsiisa**

1) Halaʻʻlinyisi fulonni biddisinni gumulamanno gorsu waa masmarunni bebbeehate owaante ijaarsate hossanno baatto xiinxallote badoonni baycho huxxame agarama noose.
2) Gorsu way buicho afiʻʻnara dandiinanni base ogeessu xiinxallo kaima assatenni qoqowame ofolla noose.

**63.የመስኖ ውሃ መገኛ ቦታን እና አካባቢውን ማስተዳደርና መንከባከብ**

ማንኛውም የመስኖ ውሃ ኢንተርፕራይዝ ወይም ማህበር የሚከተለው መብትና ሀላፊነት ይኖረዋል፡

1) የመስኖ ውሃ ምንጭ መገኛ ቦታን ማስተዳደር፣ መንከባከብ እና በአግባቡ መያዝ እንዲሁም ለውሃ ምንጭ መጎልበት የሚረዱ ተክሎችን በውሃ ምንጩ አካባቢ መትከል፤
2) ጉዳዩ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን የመስኖ ውሃ ምንጭ ክልልን ከልሎ መያዝ፤
3) በተከለለው የመስኖ ውሃ ምንጭ አካባቢ ውሃን የሚያደርቁ ተክሎች እንዳይተከሉ መከልከል፤ እና
4) ከተከለለው የመስኖ ውሃ ምንጭ አካባቢ ተክሎችን ማውደም፣ መቁረጥን እና የተለያዩ ግንባታዎች እንዳይካሄዱ መከልከል አለበት።

**64.የመስኖ ውሃ ኢንተርፕራይዝ ወይም ማህበር ይዞታን ማስከበር**

1) ስፋቱ በሚወጣው ደንብ የሚወሰን የመስኖ ውሃ በመስመር ማከፋፈያ አገልግሎት ለመገንባት የሚውል መሬት በጥናት በተለየው ስፍራ ተከብሮ መጠበቅ አለበት::
2) የመስኖ ውሃ ምንጭ ሊገኝ የሚችልበት ሥፍራ በባለሙያ ጥናት ላይ በመመስረት ተከልሎ መቀመጥ አለበት::

## GAFA SASE

## XAPHOOMU GADACHO, EJENSETE FAJJO HASIDHANNO HAJUBBANNA AMADAMA NOONSA TAJUBBA

**65. Interpiraayizete woy Maamarrate Xaphoomu Gadacho**

1) Aye innterpiraayize woy maamarra tenne wodhonni woy wolootu seerinni tungoonni gadacho noo gedeenni owaante uyinanni harinsho giddo konni woroonni no gadacho heedhanonsa:
   (a) Hasiishshu garinni farote noo olluubara woy woraddara gorsu waa afi"dhanno gede irkkisa;
   (b) Danchu assooti loosssa aana beeqqa;
   (c) Wolootu dagoomu millimillo giddo beeqatenni dagoomu yawonsa fula.
2) Konni quwira cinaancho quwa (1) hunda worroonnihu jeefishshi gari biddisunni gumulamanno.

**66. Ejensete Fajjo Hasidhanno Hajubba**

1) Aye interpiraayize woy maamari konni woroonni noo assootubba loosate Ejensetewiinni balaxxe borrote fajjo afira noonsa:
   (a) Interpiraayizete woy maamaru galtinote wodho woyyeessate;
   (b) Interpiraayizete woy maamaru owaantete qoqqowo woyyeessate;
   (c) Interpiraayizete woy maamaru jajji asalunni amadamanno gede aate woy amadisiisate;
   (d) Mittu interpiraayizete woy maamaru

## ክፍል ሰባት

## ጠቅላላ ግዴታዎች፤ የኤጀንሲውን ፍቃድ የሚሹ ጉዳዮች እና መያዝ ስላለባቸው መዝገቦች

**65.የኢንተርፕራይዝ ወይም የማህበር ጠቅላላ ግዴታዎች**

1) ማንኛውም ኢንተርፕራይዝ ወይም ማህበር በዚህ ደንብ ወይም በሌሎች ሕጎች የተጣለበትን ግዴታ እንደተጠበቀ ሆኖ በአገልግሎት አሰጣጥ ሂደት ውስጥ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩታል፤

(ሀ) እንደስፈላጊነቱ አጎራባች ቀበሌዎች ወይም ወረዳዎች የመስኖ ውሃ እንዲያገኙ መደገፍ፤

(ለ) በበጎ አድራጎት ስራዎች ላይ መሳተፍ፤

(ሐ) በሌሎች ማህበራዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ በመሳተፍ ማህበራዊ ኃላፊነታቸውን መወጣት።

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ሥር የተደነገገው ድንጋጌ አፈጻጸም ሁኔታ በመመሪያ ይወሰናል።

**66.የኤጀንሲውን ፍቃድ የሚሹ ጉዳዮች**

1) ማንኛውም ኢንተርፕራይዝ ወይም ማኀበር የሚከተሉትን ተግባራት ለማከናወን ከኤጀንሲው በቅድሚያ የጽሑፍ ፍቃድ ማግኘት አለበት፤

(ሀ) የኢንተርፕራይዙን ወይም የማኅበሩን መተዳደሪያ ደንብ ለማሻሻል፤

(ለ) የኢንተርፕራይዙን ወይም የማኅበሩን የአገልግሎት ክልል ለማሻሻል፤

(ሐ) የኢንተርፕራይዙን ወይም የማኅበሩን ንብረቶች በመያዣነት ለመስጠት ወይም ለማስያዝ፤

(መ) የአንድን ኢንተርፕራይዝ ወይም ማኀበር

miili gorsu wau horaamesimmate qoososi rigidantanno gede assate.

2) Ejense konni quwi cinaancho quwa (1) fidalete kiiro (a) kasise (d) garinni shiqqanno fajjote xa’mora 15 barra roorinokki yanna giddo dawaro aa noose. Tittirshu jeefishshi biddisunni gumulamanno.

**67. Interpiraayize woy Maamarra Amada Noonsa Tajubba**

Aye interpiraayize woy maamarra konni woroonni noo tajubba amada noonsa:

1) Owaantete qoqqowo leelishano kaarta;
2) Gorsu waa horonsirate uyinooninsa owaantete fajjo;
3) Hasiishshu garinni sasu sasu aganinni haaronsinanni miillate tittironna mittu mittunku miili baatote amadooshshi hala’linyenna afantanno base tittirshunni amaddinno miillate taje;
4) Interpiraayize woy maamaru adhanno woy fushshanno gorsu way bikka xawisanno taje;
5) Miilla afidhanno way bikka leellishanno taje woy mittu mittunku miili gorsu baatto haayikisate adhitinosi sa’atenna mageeshshi yannara haayikisinoro leellishshanno taje;
6) Miilla baattinokkihanna baattino mareekamate, gatamarshu, looso harisate, gorsu waye owaantenna woloota baatooshubba leellishshanno taje;
7) Bordete, xaphoomu songonna loosu jefisiisancho komite gambooshubba

አባል የውኃ ተጠቃሚነት መብት እንዲሰረዝ ለማድረግ፡፡

2) ኤጀንሲው በዚህ አንቀጽ ንዐስ አንቀጽ (1)ከፊደል ተራ ቁጥር (ሀ)እስከ ፊደል ተራ ቁጥር (መ) መሠረት ለሚቀርብ የፈቃድ ጥያቄ ከ15 ቀን ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ምላሽ መስጠት አለበት፡፡ ዝርዝር አተገባበሩ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

**67.ኢንተርፕራይዞች እና ማህበራት መያዝ ስላለባቸው መዛግብት**

ማንኛውም ኢንተርፕራይዝ ወይም ማኅበር የሚከተሉትን መዛግብት መያዝ አለበት፤

1) የአገልግሎት ክልልን የሚያሳይ ካርታ፤
2) የመስኖ ውሃውን ለመጠቀም የተሰጣቸው የአገልልግሎት ፍቃድ፤
3) እንደአስፈላጊነቱ በየሦስት ወሩ የሚታደስ የአባላትን ዝርዝር እና የእያንዳንዱን አባል የመሬት ይዞታ ስፋት እና የሚገኝበትን ቦታ በዝርዝር የያዘ የአባላት መዝገብ፤
4) ኢንተርፕራይዙ ወይም ማኅበሩ የሚቀበለውን ወይም የሚያወጣውን የውሃ መጠን የሚገልጽ መዝገብ፤
5) አባላት ያገኙትን የውሃ መጠን የሚያሳይ መዝገብ ወይም እያንዳንዱ አባል የመስኖ መሬቱን ለማጠጣት የፈጀበት ሰዓትና ለስንት ጊዜ እንደጠጣ የሚያሳይ መዝገብ፤
6) አባላት ያለባቸውንና የፈፀሟቸውን የመመዝገቢያ፣የጥገና፣ ሥራ ማስኬጃ፣የመስኖ ውሃ አገልግሎት እና ሌሎች ክፍያዎችን የሚያሳይ መዝገብ፤
7) የቦርድ፣ ጠቅላላ ጉባኤና የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስብሰባዎች ቃለ-ጉባኤዎችን የያዘ

songaale amaddino taje;

8) Jeefinsoonni hironna sheemata amaddino taje;

9) Jajju kiiro assinoonni taje;

10) Interpiraayize woy maamaru horonsiranno gorsu du'namanno awutaare aana assinoonni qorqorshubba, xiinxallubbanna doogga amaddino taje;

11) Assinoonni gatamarsha leellishshanno taje;

12) Halaalnyanna wo''ma shallagote tajubbanna woxe amaddino sanade;

13) Interpiraayize woy maamaru galtinote wodhora tittiroonni woloota tajubba amada noonsa.

**68. <u>Ejense Amada Noose Taje</u>**

1) Ejense Interpiraayizetenna gorsu way horaameyye maamarra taje qixxeessanno, amadanno;

2) Ejense amaddanno taje mitte mittente Interpiraayizenna maamarra lainohunni ajay ajeenna konni woroonni tittirshu mashalaqqe amada noose:

   (a) Interpiraayize woy maamaru su'manna teesso;

   (b) Mitte mittente interpiraayize woy maamarra mareekantino kiironna mareekantino barra;

   (c) Owaantete qoqqowi hala'linyenna afamanno base;

   (d) Miillate kiiro;

መዝገብ፤

8) የተፈፀሙ ግብይቶችንና ውሎችን የያዘ መዝገብ፤

9) የንብረት ቆጠራ የተደረገበት መዝገብ፤

10) ኢንተርፕራይዙ ወይም ማኅበሩ በሚጠቀምበት የመስኖና ድሬኔጅ አውታር ላይ የተደረጉ ቁጥጥሮችን፣ጥናቶችን እና ቅያሶችን የያዘ መዝገብ፤

11) የተካሄዱ ጥገናዎችን የሚያሳይ መዝገብ፤

12) ትክክለኛና የተሟላ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች፤ እና

13) በማኅበሩ ውስጠ-ደንብ የተዘረዘሩ ሌሎች መዝገቦች መያዝ አለበት፡፡

**68. <u>ኤጀንሲው መያዝ ስላለበት መዝገብ</u>**

1) ኤጀንሲው የኢንተርፕራይዞችን እና የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ማኅበራትን መዝገብ ያቋቁማል፣ይይዛል፤

2) ኤጀንሲው የሚይዘው መዝገብ ስለእያንዳንዱ ኢንተርፕራይዝ እና ማኅበር ቢያንስ የሚከተለትን ዝርዝር መረጃዎች መያዝ አለበት፤

(ሀ) የኢንተርፕራይዙን ወይም የማኅበሩን ስምና አድራሻ፤

(ለ) የእያንዳንዱን ማኅበር የምዝገባ ቁጥር እና የተመዘገበበትን ቀን፤

(ሐ) የአገልግሎት ክልሉን ስፋትና የሚገኝበትን ቦታ፤

(መ) የአባላቱን ቁጥር፤

(e) Loosu harisaanchi, loosu jefisiisancho komite miilla, gambisaanchunna borreesaanchu su’ma, teessonna bilbilu kiiro;

(f) Interpiraayize woy maamaraho sayinsoonni mootimmate xintu latishshi amadooshshi heeriro konne leellishshanno tittirshu mashalaqe.

3) Interpiraayize woy maamaru miilla ejensete uurrinsoonni taje hiite loosu yannarano la’’ate qoosso noonsa.

**GAFA SETTE**

**GORSU DU’NAAMANCHI OWAANTE AWUTAARE LAINOHUNNI**

**69. Yannite Gorsu Du’namaanchi Awutaare Saayisa Lainohunni**

1) Mitte yannite gorsu du’namaanchu awutaare qoqqowu mootimmanna mootimmannita ikkitinokki urrinshubba fulonni ijarsiniro woy marro haaroonsiniro tenne gorsu du’namaanchi awutaare wo’ma woy gama gola mitte interpiraayize woy maamaru owaantete qoqqowi giddo fulo qolsiisate wodhi-woro harunsite Ejense interpiraayizete woy maamaru ledo iillitanno sumuumme garinni horote aana hossanno qoosso interpiraayizete woy maamaraho sayissara dandiitanno.

2) Mitte interpiraayize woy maamari owaantete qoqqowi giddo qoqqowu mootimanni mootimmannita ikkitinokki

(ሠ) የስራ እስኪያጁን፣ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴውን አባላት፣ የሰብሳቢውንና የፀሀፊውን ሥም፣ አድራሻና የስልክ ቁጥር፤

(ረ) ለኢንተርፕራይዙ ወይም ለማኅበሩ የተላለፈ የመንግስት መሠረተ ልማት ይዞታ ካለ ይህንኑ የሚያሳዩ ዝርዝር መረጃዎች::

3) የኢንተርፕራይዙ ወይም የማኅበሩ አባላት በኤጀንሲው ዘንድ የተቋቋመውን መዝገብ በማናቸውም መደበኛ የሥራ ሰዓት የማየት መብት ይኖራቸዋል።

**ክፍል ስምንት**

**ስለመስኖና ድሬኔጅ አውታሮች**

**69.ዘመናዊ የመስኖና ድሬኔጅ አውታሮችን ስለማስተላለፍ**

1) አንድ ዘመናዊ የመስኖና ድሬኔጅ አውታር በክልሉ መንግስት እና መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ወጪ ከተገነባ ወይም መልሶ ከታደሰ የዚህ መስኖና ድሬኔጅ አውታር ሙሉ ወይም የተወሰነ ክፍል በአንድ ኢንተርፕራይዝ ወይም ማኅበር አገልግሎት ክልል ውስጥ የሚገኝ ወጪን የማስመለስ መርህን ተከትሎ ኤጀንሲው ከኢንተርፕራይዙ ወይም ከማኅበሩ ጋር በሚደረሰው ስምምነት መሠረት በጥቅም ላይ የሚውልበትን መብት ለኢንተርፕራይዙ ወይም ማኅበሩ ሊያስተላልፍ ይችላል፤

2) አንድ ኢንተርፕራይዝ ወይም ማኅበር በአገልግሎት ክልል ውስጥ በክልሉ መንግስት እና መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ወጪ

urrinshubba fulonni ijarsiniro woy marro haaroonsinoonni yannite gorsu du'namaanchu awutaare gama gola horonsirate qoosso gumulantinokki yannara sayinse uyinannise gede Ejensete woy Ejensete hundaancho ikkino bisira ku'la dandiitanno.

3) Way shiqinshaniwi afamano baychi kofatto, way du'namanno raga soorisiinsanniha, paampite xaawi woy wole dana xintu latishshi mitte interpiraayize woy maamari owaantete qoqqowi giddo afamannoha ikkiro waa lagunni, daadanno wayinni, corraniwiinni, biuchotenni woy wole kalaqamunni afamannowiinni haarate horonsinanni xintu latishshi interpiraayizete woy maamaraho owaante aa dandaanno gede sayinsara dandiinanni.

4) Gorsu du'namaanchi awutaare saayinsanni sumuummete sanade bikkantino qitsenni ikkite:

(a) Sayinsanni gorsu du'namaanchi awutaare noo gara leellishanno tittirshu mashalaqe; nna

(b) Xintu latishshi gatamaarsha lainohunni sumuumme assitinohu bissa noonsa qoossonna gadacho kamaalannoha ikka noosi.

5) Ejense interpiraayizete woy maamarrate sayinsoonikkinna umise qorqorshi hunda

የተገነባ ወይም መልሶ የታደሰ ዘመናዊ የመስኖ ድሬኔጅ አውታር የተወሰነ ክፍል የተጠቃሚነት መብት ላልተወሰነ ጊዜ ተላልፎ እንዲሰጠው ለኤጀንሲው ወይም ለተዋረድ አካል ማመልከት ይችላል፤

3) የውሃ አቅርቦት መገኛ ቦታ ግድብ፣የውሃ መጥለፊያ ውቅር፣የፓምፕ ጣቢያ ወይም ሌላ ዓይነት መሠረተ ልማት በአንድ ኢንተርፕራይዝ ወይም ማኀበር የአገልግሎት ክልል ውስጥ የሚገኝ የሆነ እንደሆነ ውሃውን ከወንዝ፣ ከጅረት፣ ከማጠራቀሚያ፣ ከኩሬ ወይም ከሌላ ተፈጥሯዊ መገኛ ለመውሰድ የሚያገለግለው መሠረተ-ልማት ለማኀበሩ አገልግሎት መስጠት እንዲችል ሊተላለፍ ይችላል፤

4) የመስኖና ድሬኔጅ አውታር ማስተላለፊያ ስምምነት ሰነዱ በተወሰነ ቅጽ ሆኖ፤

(ሀ) የሚተላለፈው የመስኖና የድሬኔጅ አውታር ያለበትን ሁኔታ የሚያሳይ ዝርዝር መረጃ፤ እና

(ለ) የመሠረተ ልማቱን ጥገና አስመልክቶ ስምምነት ያደረጉት ወገኖች ያላቸውን መብቶችና ግዴታዎች፤ የሚያካትት መሆን አለበት።

5) ኤጀንሲው ለኢንተርፕራይዞች ወይም ለማህበራት ያልተላለፈና በራሱ ቁጥጥር ስር የሚገኙ የመስኖና ድሬኔጅ አውታር የተወሰኑ

afantanno gorsu du’namaanchi awutaare gamu goli heeriro garunni agarrenna gatamarsite amadansa buuxate yawo noose.

**70. <u>Budu Gorsu Du’namaanchi Awutaare Horonsi’nanni Afanshu Woraqata</u>**

1) Mitte interpiraayize woy maamari owaantete qoqqowi giddo afantanno budu gorsu du’namaanchi awutaare lainohunni horonsirate afanshu woraqata uyinaninsa gede qorqorano bisira ku’laato shiqisha dandiitanno.
2) Horonsirate afanshu woraqati budu gorsu du’namaanchi awutaare qara qara ikkitino xawishubba amadannohanna interpiraayize woy maamaru awutaare horonsirate noosi qoosso buuxisiisannoha ikkanno.

**71. <u>Mashalaqe Sayisa Lainohuninna Tekiniikete Qorqorsha</u>**

1) Mittee interpiraayize woy maamari sayinsoonnisi gorsunna du’nmaanchu awutaare gatamarshanna afantanno gara Ejensete yanite mashalaqe aa noosi.
2) Ejensete widoonni biilloonye uyinoonisi aye loosaasinchi owaantete qoqqowi eatenni interpiraayizete woy maamaraho sayinsoonni gorsunna du’namaanchu awutaare noo gara qorqortara dandiitanno.
3) Ejensetenni riqiwamino loosaasinchi qorqorsha assi gedensaanni anfoonni mashala garinni:

ክፍሎች ቢኖሩ በሚገባ ተጠብቀውና ተጠግነው መያዛቸውን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፡፡

**70. <u>የባሕላዊ መስኖና ድሬነጅ አውታር መጠቀሚያ የምስክር ወረቀት</u>**

1) አንድ ኢንተርፕራይዝ ወይም ማህበር በአገልግሎት ክልሉ ውስጥ ስለሚገኝ ባሕላዊ የመስኖና ድሬኔጅ አውታር በሚመለከት የመጠቀሚያ ምስክር ወረቀት እንዲሰጠው ለተቆጣጣሪ አካል ማመልከት ይችላል፡፡
2) የመጠቀሚያ ምስክር ወረቀቱ የባህላዊ መስኖና ድሬኔጅ አውታሩን ዋና ዋና የሆኑ መግለጫዎችን የሚይዝና ማህበሩ በአውታሩ ለመጠቀም ያለውን መብት የሚያረጋግጥ ይሆናል፡፡

**71. <u>መረጃን ስለማስተላለፍና ስለቴክኒክ ቁጥጥር</u>**

1) አንድ ማኅበር ስለተላለፈለት የመስኖና የድሬኔጅ አውታር ጥገናና ስለሚገኝበት ሁኔታ ለኤጀንሲው ወቅታዊ መረጃ መስጠት አለበት፤
2) በኤጀንሲው አማካኝነት ሥልጣን የተሰጠው ማንኛውም ሠራተኛ ወደ አገልግሎት ክልል በመግባት ለኢንተርፕራይዙ ወይም ለማኅበሩ የተላለፈው የመስኖና የድሬኔጅ አውታር ያለበትን ሁኔታ ሊቆጣጠር ይችላል፤
3) በኤንሲው የተወከለው ሠራተኛ ቁጥጥር ካደረገ በኋላ በተገኘው መረጃ መሠረ፤

(a) Gorsu du'namaanchi awutaare aana gawajjo woy huno iillitanokki gede; woy

(b) Gorsu du''namaanchi awutaare horonshi korkaatinni mootimmate woy sayikki bissa jajji aana gawajjo iillitanokki gede, hajote winaamimma gede gama loossa loosantanno gede interpiraayize woy maamara hajajara dandaanno.

**72. Jajju Owaante Lainohunni**

Mitte interpiraayize woy maamari miillate horora hasiissannoha ikke leelliro gorsunna du'nmaanchu awutaare haroonsate woy latisate mitte baatto owaante afira hasiisannote ikkituro Ejensetenni adhamooshshe afidhuronna garimma noosi seeri garinni baattote annira kiiso balaxe baatturo fajjinaninsa.

**GAFA SETTE**

**EO, WOXENNA JAJJU GASHSHOOTI AMURAATE**

**73. Interpiraayizete woy Maamaru Eote Buicho**

1) Interpiraayize woy maamarra uminsa eonni galtanno.

2) Interpiraayize woy maamarrate eote bua aantete noorinni ikkitanno:

(a) Gorsu way owaante loossanni afi"nanni eonni;

(b) Gorsu way tekinikete owaante aate loosanni afi"nanni baatoshshe;

(c) Baraa"rshunna kaa"lote garinni

(ሀ) በመስኖና በድሬኔጅ አውታሩ ላይ ጉዳት ወይም ጥፋት እንዲይደርስ፤ ወይም

(ለ) በመስኖና ድሬኔጅ አውታሩ አጠቃቀም ምክንያት በመንግሥት ወይም በሦስተኛ ወገኖች ንብረት ላይ ጉዳት እንዳይደርስ፣ እንደጉዳዩ አስቸኳይነት የተወሰኑ ሥራዎች እንዲከናወኑ ማኅበሩን ሊያዝ ይችላል፡፡

**72.ስለንብረት አገልግሎት**

አንድ ኢንተርፕራይዝ ወይም ማኅበር ለአባላቱ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የመስኖና ድሬኔጅ አውታሩን ለማደስ ወይም ለማልማት የአንድን መሬት አገልግሎት ማግኘት አስፈላጊ ሲሆን በኤጀንሲው ተቀባይነት ሲያገኝ እና አግባብ ባለው ህግ መሠረት ለባለመሬቱ ካሳ አስቀድሞ ሲከፈል ይፈቀድለታል፡፡

**ክፍል ስምንት**

**የገቢ፣የገንዘብና የንብረት አስተዳደር ሥርዓት**

**73.የኢንተርፕራይዝ ወይም ማህበር የገቢ ምንጭ**

1) ኢንተርፕራይዝ ወይም የተጠቃሚዎች ማህበር በራሱ ገቢ ይተዳደራል::

2) የኢንተርፕራይዙ ወይም ማህበሩ የገቢ ምንጭ ከሚከተሉት ይሆናል፡

(ሀ) ከመስኖ ውሃ አገልግሎት ስራዎች የሚገኝ ገቢ፤

(ለ) ከመስኖ ውሃ የቴክኒክ አገልግሎት አሰጣጥ ስራዎች የሚገኝ ክፍያ፤

(ሐ) በስጦታ ወይም በእርዳታ መልክ የሚገኝ

afi''nanni woxe;

(d) Maashinerete woy ijaarshunni, haru, uduunnu magaazinenna woloota jajjubba kira aate waaginni afi''nanniha;

(e) Owaantete yannansa guddino jajjuwa hironni afi''nanni woxe;

(f) Seera sa''inno bissa aana gumullanni qorichinni e''anno eo;

(g) Wolootu aye buichonni afi''nanni eonni ikkanno.

3) Konni quwi cinaancho quwa (2) hunda worroonnihu hee''rirono, gorsu way owaante uurrisatenna halashshate Qoqqowu Mootimma woy woradu gahshsooti dhukinsa gara xinxallate hasiisanno irko assitara dandiitanno.

**74. <u>Woxunna Shallagote Taje Horoonsishshinna Gashshooti Amuraate</u>**

1) Interpiraayize woy maamaru tenne wodhora quwa 73 garinni gamba assinanni eo mixi''noonni hexxora hosiisa noosi.

2) Interpiraayize woy maamaru ivestimentete fultino fulo qolsiisate diriirsinoonni amuraate harunsatenni tenne hajora fananni baankete shallago kiiro giddo yanna yannatenni eo assa noosi. Tittirshu jeefishshi fulanno biddisinni gumulamannoha ikkanno.

ገንዘብ፤

(መ) ከማሽነሪ ወይም ህንጻ፣ አዳራሽ፣ ከዕቃ መጋዘን እና ሌሎች ንብረቶች ኪራይ ዋጋ የሚገኝ፤

(ሠ) የአገልግሎት ጊዜያቸውን ከጨረሱ ንብረቶች ሽያጭ የሚገኝ ገንዘብ፤

(ረ) ህግ በተላለፉ አካላት ላይ ከሚወሰን ቅጣት የሚገባ ገቢ፤

(ሰ) ከሌሎች ማንኛውም ምንጮች የሚገኝ ገቢ ይሆናል፡፡

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ስር የተደነገገው ቢኖርም፣ የመስኖ ውሃ አገልግሎቶችን ለመመስረትና ለማስፋፋት የክልሉ መንግስት ወይም የወረዳ አስተዳደሩ የአቅማቸውን ሁኔታ በማጥናት አስፈላጊውን ድጋፍ ሊያደርግላቸው ይችላል፡፡

**74.<u>የገንዘብ እና የሒሳብ መዝገብ አጠቃቀምና አስተዳደር ሥርዓት</u>**

1) ኢንተርፕራይዙ ወይም ማህበሩ በዚህ ደንብ አንቀጽ 73 መሰረት የሚሰበሰበውን ገቢ ለታቀደው ዓላማ ማዋል አለበት::

2) ኢንተርፕራይዙ ወይም ማህበሩ ለኢንቨስትመት የወጡ ወጪዎችን ለማስመለስ የተዘረጋውን ስርዓት በመከተል ለዚሁ ጉዳይ በሚከፈተው የባንክ ሂሳብ ቁጥር ውስጥ በየዓመቱ ገቢ ማድረግ አለበት፡፡ ዝርዝር አፈጻጸሙ በሚወጣው መመሪያ የሚወሰን ይሆናል፡፡

3) Interpiraayize woy maamaru gamba assinanni eo su"misinni fananni baankete shallagote kiiro giddo eo assa noosi.
4) Interpiraayize woy maamaru halaalanyanna wo"ma shallagote taje heedhanosi.
5) Barru loosu millimillora hassanno woxu bikka boorde woy maamaru fushshanno biddisinni gumulamannoha ikkano.
6) Aye bisi gorsu way interpiraayizooti woy maamarra baajette urrinshate hexxo gobbaanni wole owaantera hossanno gede assate biilloonyi dinonsa.
7) Aye gorsu way interpiraayize woy maamari looso harinsanniha, damoozunna uduunnu gatamarshi woy riqiwo fulo gadacho noosi.

**75. <u>Odiitete Buuxo</u>**

1) Interpiraayizubbanna maamarra shallagonsa yanna yannate odiite assate giddooyidi odditete amuraate diriirsitanno.
2) Interpiraayizetenna maamaru shallagote buuxo dirunni mitte higge odiite assate fajjo noosi bisinni jeefama noose.
3) Konni quwi cinaancho quwa (1) hunda worroonnihu noo gedeenni, hasiisannoha ikke leelliro biilloonyu noosi bisi aye yannara uurrinshatenna maamaru shallago

3) ኢንተርፕራይዙ ወይም ማህበሩ የሚሰበሰበውን ገቢ በስሙ በሚከፈተው የባንክ ሂሳብ ውስጥ ገቢ ማድረግ አለበት::
4) ኢንተርፕራይዙ ወይም ማህበሩ ትክክለኛ እና የተሟላ የሂሳብ መዛግብት ይኖረዋል::
5) ለቀን የስራ እንቅስቃሴ የሚውለው የገንዘብ መጠን ቦርዱ ወይም ማህበሩ በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰን ይሆናል::
6) ማንኛውም አካል የውሃ ኢንተርፕራይዞችን ወይም ማህበራትን በጀት ከድርጅቱ ዓላማ ውጪ ለሌላ አገልግሎት እንዲውል የማድረግ ስልጣን የለውም::
7) ማንኛውም የመስኖ ውሃ ኢንተርፕራይዝ ወይም ማህበር የስራ ማስኬጃ፣ የደመወዝ እና የመሳሪያዎች ጥገና ወይም መተኪያ ወጪን የመቻል ግዴታ አለበት።

**75.<u>የኦዲት ምርመራ</u>**

1) ኢንተርፕራይዞች እና ማህበራት ሒሳቦቻቸውን በየጊዜው ኦዲት እንዲደረግ የውስጥ ኦዲት ሥርዓት ይዘረጋሉ።
2) የኢንተርፕራይዙ እና የማህበሩ ሂሳብ ምርመራ በዓመት አንድ ጊዜ ኦዲት የማድረግ ፈቃድ በተሰጠው አካል መፈጸም አለበት::
3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ስር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ስልጣን ያለው አካል በማንኛውም ጊዜ በኢንተርፕራይዙ እና በማህበሩ ሂሳብ ላይ

aana buuxo assara dandaanno.

**76. Jajju Gashshoote**

Aye interpiraayize woy maamari gorsu waa corate, bebbeehatenna wole owaante aate hossanno uduunne, maashinere, ijaarshu gumanna babbaxxitino jajjuwa maarekatenni annimatenni gashsha, towaatanna agara noose.

**77. Hirotenna Jajju Gashshooti Amurate**

1) Aye interpiraayize woy maamarra hirotenna jajju gashshooti amurati massagamannohu mootimmate hirotenna jajju gashshooti lallawi garinni ikkanno.
2) Konni quwira cinaanchu quwi (1) worroonihu heerirono urrinshshanna maamarra lallawunni diriirsinoonni amurate agarte hiro jeefisa dandiitanokki gari xaadiro hiro baxxino garinni jeefisa dandiitanno loosu harinsho lainohunni biiro biddisa fushshitanno.
3) Konni quwira cinaancho quwa (2) worroonihu heerirono interpiraayizubanna maamarra lallawunni diriirsinoonni amurate agarte hiro jeefisa dandiitannohu baxxinno garinni hirraanni hirote amurate borde kaajishurooti; ikkollana harancho yanna giddo borde gamba yaa hoogguro tonnu

ምርመራ ሊያደርግ ይችላል፡፡

**76. የንብረት አስተዳደር**

ማንኛውም ኢንተርፕራይዝ ወይም ማህበር ለመስኖ ውሃ ማጠራቀሚያ፣ ማከፋፈያ እና ለሌላ አገልግሎት አሰጣጥ የሚውሉ መሳሪያዎችን፣ ማሽነሪዎችን፣ የግንባታ ውጤቶችን እና የተለያዩ ንብረቶችን በመመዝገብ በባለቤትነት ማስተዳደር፣ መንከባከብ እና መጠበቅ አለበት፡፡

**77. የግዢ አፈጻጸም እና ንብረት አስተዳደር ሥርዓት**

1) ማንኛውም የኢንተርፕራይዞች እና የማህበራት የግዥ እና ንብረት አስተዳደር ሥርዓት የሚመራው በክልሉ የመንግስት የግዥ እና ንብረት አስተዳደር አዋጅ መሰረት ይሆናል፡፡
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም ድርጅቶችና ማህበራት በአዋጁ የተዘረጋውን ስርዓት ጠብቀው ግዥ መፈጸም የማይችሉበት ሁኔታ ሲያጋጥም ግዥውን በልዩ ሁኔታ መፈጸም የሚችሉበት የአሰራር ስርዓት በተመለከተ ቢሮው መመሪያ ያወጣል፡፡
3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገው ቢኖርም በአዋጁ የተዘረጋውን ስርዓት ጠብቀው ግዥ መፈጸም የማይችሉበት ሁኔታ ሲያጋጥም ግዥውን በልዩ ሁኔታ መፈጸም የሚቻልበትን አሰራር ቦርዱ ማፅደቅ አለበት፤ ሆኖም ቦርዱ በአጭር ጊዜ መሰብሰብ ባይችል በአስር ተከታታይ ቀናት ውሥጥ ግዥው

aantetenni kiiranni barri giddo hiro borde kaajisha noose.

4) Konni quwi cinaanchu quwi (2) jeefishira kalaqamunni woy hedeweelicho owaante aa agurturo woy mannu loosino danonni gorsu way doogo, gorsu way afamannowa, corraniwa woy gorsu waa laashshate woy bebbeehate ka"lano elekitro mekanikaalete uduuni aana gawajjo iilitenna gorsu way shiqo gamunni woy wo"munni wo"ma urrituro owaante rahotenni hanafisiisate jeefinsani winaamu hiro interpirayizete maajimente woy loosu jefisiisancho komitenni gumulisiisanni hiro jeefisa dandiitanno.

**78. <u>Mannu Jiro Gashshoote</u>**

1) Gorsu way interpiraayize woy maamarrate mannu jiro gashshooti loosiisannohunna loosaasinchu hajo lallawi garinni jeefamannoha ikkanno.
2) Interpiraayizetenna maamarrate uminsata ikkitino mannu jiro tantanonna damoozu bikki hee"rannonsa.
3) Konni quwi cinaancho quwa (2) hunda worroonnihu noo gedeenni interpiraayizete woy maamaru loosaasine damoozi Ejense xiinxallote aana xintamatenni qixxeesitanno isikeele garinni boordetenni woy loosu jefisiisancho komitenni jeefamannoha ikkanno.
4) Loosaasinete damoozi woy babbaxxitino horo lexxo assa hasiisannota ikkite leelturo

በቦርዱ መፅደቅ አለበት።

4) ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) አፈፃፀም በተፈጥሮ ወይም በድንገተኛ ብልሽት ወይም በሰው ሰራሽ አደጋ ምክንያት የመስኖ ውሃ መስመር፣ የመስኖ ውሃ መገኛ፣ ማጠራቀሚያ ወይም የመስኖ ውሃን ለማከፋፈል የሚረዳ የኤሌክትሮ-ሜካኒካል መሣሪያዎች ጉዳት ደርሶባቸው የመስኖ ውሃ አቅርቦት በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ ከተቋረጠ አገልግሎቱን በአፋጣኝ ለማስጀመር የሚፈፀም አፊጣኝ ግዥ በተቋሙ ማኔጅመንት ወይም ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ እያስወሰኑ ግዢ መፈጸም ይችላሉ።

**78.<u>የሰው ሀብት አስተዳደር</u>**

1) የመስኖ ውሃ አገልግሎት ኢንተርፕራይዝ እና ማህበር የሰው ሀብት አስተዳደር በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ መሰረት የሚፈጸም ይሆናል::
2) ኢንተርፕራይዝ እና ማህበር የራሱ የሆነ የሰው ሀብት መዋቅርና የደመወዝ ስኬል ይኖረዋል::
3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ስር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ኢንተርፕራይዝ እና ማህበር ሰራተኞች ደመወዝ ኤጀንሲው በጥናት ላይ በመመስረት በሚዘጋጀው ስኬል መሰረት እና ቦርደ ባፀደቀው አግባብ የሚፈጸም ይሆናል።
4) ጥቅማ ጥቅሞች ጭማሪ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ቦርዱ ወይም የስራ አስፈጻሚ

boorde woy loosu jefisiisaano komite Ejense qixxeessitanno damoozu isikeele xaara sa"aukkinni jeefisa dandiitanno.

5) Loosiisanohunna loosaasinchu hajo lallawinni hanqafantannokki loosu massaggaanno qixire, gaamooshshi, lophonna loosunni geegiissa fulanno biddisi garinni jeefamannoha ikkanno.

6) Interpiraayize woy maamaru dirunni afidhanno buuxamino tirfe kaima assatenni loosaasine jawaachishate diru goofimarchira bikkisi boordetenni woy loosu jefisiisancho komitenni gumulamanno ledote baatooshshe loosaasinete baattara dandiitanno.

## GAFA HONSE

## GASHSHOOTU XA'MAMOOSHSHENNA KOFFEENYA SHIQINSHANNI GARA

### 79. Gashshootu Hunonna Qoricha

1) Aye owatamaanchi aantino assootuwa loose leelliro, interpiraayize woy maamaru hajote garinni woxu qorichinni sheemaate woy owaante agurate iillitanno gahshsootu qaafo adhara dandaanno:

   (a) Interpiraayizete woy maamaru galtinote wodho ayirisinokkiha ikkiro;

   (b) Galtinote wodhoninna tenne wodho garinni gumuloonni baatooshshe yannatenni baatinokkiha ikkiro, woy hasii'noonni yannar wolqate loosi kaa'looshshe assinokkiha ikkiro;

ኮሚቴው ኤጀንሲው የሚያዘጋጀውን የደሞዝ ስኬል ጣሪያ ሳያልፍ መፈጸም ይችላል::

5) በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ የማይታቀፉ የስራ መሪዎች ቅጥር፣ ምደባ፣ እድገት እና ከስራ ማሰናበት በሚወጣው መመሪያ መሰረት የሚፈጸም ይሆናል::

6) ዜንተርፕራይዙ ወይም ማህበሩ በዓመት በሚያገኘው የተጣራ ትርፍ ላይ በመመስረት ሰራተኞቹን ለማበረታታት በዓመቱ መጨረሻ ላይ መጠኑ በቦርዱ ወይም በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው የሚወሰነውን ተጨማሪ ክፍያ ለሰራተኞቹ ሊከፍል ይችላል።

## ክፍል ዘጠኝ

## አስተዳደራዊ ተጠያቂነት እና የቅሬታ አቀራረብ ሥርዓት

### 79.አስተዳደራዊ ጥፋት እና ቅጣት

1) ማንኛውም ተገልጋይ የሚከተሉትን ድርጊቶች ፈጽሞ ከተገኘ፣ ኢንተርፕራዙ ወይም ማህበሩ እንደ ጉዳዩ ክብደት ከገንዘብ ቅጣት እስከ ውል ወይም አገልግሎት ማቀረጥ የሚደርስ አስተዳደራዊ እርምጃ ሊወስድበት ይችላል፤

(ሀ) የማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ ያላከበረ እንደሆነ፣

(ለ) በመተዳደሪያው ደንቡና በዚህ አዋጅ መሠረት የተወሰኑትን ክፍያዎች በወቅቱ ያልከፈለ እንደሆነ፣ ወይም በሚያስፈልግ ጊዜ የጉልበት ሥራ አስተዋጽኦ ያላደረገ እንደሆነ፣

(c) Gorsu waa interpiraayize woy maamaru fushshino pirogiraame garinni horonsirannokkiha ikkiro;
(d) Afanni here woy de’’netenni aye interpiraayizete woy maamaru jajji wou uduunni aana iillishino gawajjora gatamarsiinsanni woy riqiwote fulo baatate fajjaalessa ikka hoogiro;
(e) Baattote woy way horonshi gara lainohunni interpiraayizete woy maamaraho garimma noose mashalaqqe aate fajjaaleessa ikka hoogiro;
(f) Interpiraayzete woy maamaru loosaasine woy interpiraayizetenni woy maamarunni hajajantino woloota mannoota gorsu doogo loosu harinshonna gatamarshu loossa harisate hasiishu garinni kameela woy uduunne haadhe hadhanno woyte baatote widira e’’annokki gede hoolonoha ikkiro;
(g) Gorsu du’’namaanchi awutaate opireeshine la’’anno tekiniikete wodho ayirisate fajjaaleessa ikka hoogiro.

2) Interpiraayze woy maamaru konni quwira cinaancho quwa (1) garinni gashshootu qaafo gumulo aanno yannara gumulo tonnu barri giddo borrotenni horaameyyete iillisha noosi.

3) Qoricha tungannihu loosu jefisiisancho komitenni ikkiro yekkeero gumultanno

(ሐ) የመስኖ ውሃን ማህበሩ ባወጣው መርሃ ግብር መሠረት የማይጠቀም ከሆነ፣

(መ) ሆነ ብሎ ወይም በቸልተኝነት በማንኛውም የማህበሩ ንብረት ወይም መሳሪያ ላይ ላደረሰው ጉዳት የማስጠገኛ ወይም የመተኪያ ወጪ ለመክፈል ፈቃደኛ ካልሆነ፣

(ሠ) ስለመሬቱ ወይም ስለውሃ አጠቃቀሙ ለማህበሩ ተገቢውን መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ ካልሆነ፣

(ረ) የኢንተርፕራይዙን ወይም የማህበሩን ሠራተኞች ወይም በማህበሩ የታዘዙ ሌሎች ሰዎች የመስኖ መስመሩን አሰራር እና የጥገና ሥራ ለማካሄድ እንደ አስፈላጊነቱ መኪናዎችን ወይም መሳሪያዎችን ይዘው ሲሄዱ ወደ መሬቱ እንዳይገቡ የከለከለ ከሆነ፣ ወይም

(ሰ) የመስኖና ድሬኔጅ አውታሩን ኦኘሬሽን የሚመለከቱ ቴክኒካል ደንቦችን ለማክበር ፈቃደኛ ካልሆነ።

2) ኢንተርፕራይዙ ወይም ማህበሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት አስተዳደራዊ እርምጃ ውሳኔ በሚሰጥበት ጊዜ ውሳኔውን በአስር ቀን ውስጥ በጽሁፍ ለተጠቃሚዎች ማድረስ አለበት።

3) ቅጣቱ የሚጣለው በሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ሲሆን ለክርክር አወሳሰን ኮሚቴ ይግባኝ ሊቀርብበት ይችላል፤ በሰራ አስኪያጅ

komitera kado shiqisha dandiinanni; loosu harisanchinni tunganni qoricha ikkiro bordete kado shiqisha dandiinanni.

**80. <u>Kofeenya Shiqishate Amuraate</u>**

1) Ayno gorsu way owaante shiqo amuraati aana kofeenyu noosi horaamessi kofeenyasi maamaru loosu jefisiisaano komite murrichira woy loosu ha՝՝risaanchi woy interpiraayizete boordera shiqisha dandaanno. Jeefishshu fulanno biddisnni gumulamannoha ikkanno.
2) Tenne wodhora quwa 79 cinaancho quwa (2) garinni gashshootu qorichi gumulo iillitinosi horaameessi koffeenyu hee՝՝risiro koffeenyasi gumulo iillitusi barrinni hanafe mittu agani giddo boordete woy loosu jefisiisaancho komitera borrote shiqisha dandaanno.
3) Konni quwi cinaancho quwa (2) garinni kofeenyu shiqinose boorde woy loosu jefisiisaancho komite kofeenyu shiqi barrinni hanaffe 15 barra roortannokki yanna giddo hajo buuxxe gumulo aa noose.
4) Konni quwi cinaancho quwa (3) garinni boorde woy loosu jefisiisaancho komite uytino gumulo aana kofeenyu noosi horaamessi kofeenyasi gumulo uyni barinni hanafe noo 60 barri giddo biilloonyu noosi yoo minira shiqisha dandaanno.

የሚጣል ቅጣት ከሆነ ደግሞ ለቦርድ ይግባኝ ሊቀርብበት ይችላል፡፡

**80.<u>የቅሬታ አቀራረብ ሥርዓት</u>**

1) ማንኛውም በመስኖ ውሃ አገልግሎት አቅርቦት ስርዓት ላይ ቅሬታ ያለው ተጠቃሚ ቅሬታውን ለማህበሩ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሊቀመንበር ወይም ለሥራ አስኪያጁ ወይም ለኢንተርፕራይዙ ቦርድ ማቅረብ ይችላል፡፡ አፈጻጸሙ በሚወጣው መመሪያ የሚወሰን ይሆናል::
2) በዚህ ደንብ አንቀጽ 79 ንዑስ አንቀጽ (2) መሰረት የአስተዳደራዊ ቅጣት ውሳኔ የደረሰው ተጠቃሚ ቅሬታ ካለው ቅሬታውን ውሳኔው ከደረሰው ቀን ጀምሮ በአንድ ወር ውስጥ ለቦርድ ወይም ለስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው በጽሁፍ ማቅረብ ይችላል፡፡
3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሰረት ቅሬታ የቀረበለት ቦርድ ወይም ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ቅሬታው ከቀረበለት ቀን ጀምሮ ከአስራ አምስት ቀን ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ጉዳዩን መርምሮ ውሳኔ መስጠት አለበት::
4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሰረት ቦርዱ ወይም ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው በሰጠው ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ተጠቃሚ ቅሬታውን ውሳኔው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ባሉት ስልሳ ቀናት ውስጥ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል፡፡

## GAFA TONNE

## ADDI ADDI WORO

**81. Baajettete Diro**

Gorsu way owaante Interpiraayizenna gorsu way horaameeyye maamari baajettete diri Maaja 1 hanafe daanno diri Ella 30 geeshsha ikkanno.

**82. Halamate Gadacho**

Aye manchi tenne wodho giddo worroonni hajubba loosu aana hosiisate hajo la''annosi bisinni xa''minannisi yannara irko aate gadacho noosi.

**83. Reekkote Woro**

1) Tini wodho kaajjitee loosu aana hosara albaanni yoote mine yekkeerote aana noo aye hajubba alba loosu aana noo seerubba garinni gumulantannoha ikkanno.
2) Konni albaanni uurritino maamarra tenne wodho garinni marro tantananta geeshsha loosonsa suffannoha ikkanno.

**84. Biddisa Fushshate Biilloonye**

Biiro tenne wodho loosu aana hosiisate biddisubba fushshitanno.

**85. Loosu Aana Hossannokki Seerubba**

Tenne wodho ledo kiphantanno wodho, biddissi woy rosamino assooti tenne wodho giddo worroonni hajubba aana jeefishshu dihee''rannonsa.

## ክፍል አስር

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**81.የበጀት ዓመት**

የመስኖ ውሃ ኢንተርፕራይዝ ወይም የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ማህበር የበጀት ዓመት ከሀምሌ 1 ጀምሮ እስከሚቀጥለው ዓመት ሰኔ 30 ድረስ ይሆናል፡፡

**82.የመተባበር ግዴታ**

ማንኛውም ሰው በዚህ ደንብ ውስጥ የተደነገጉትን ጉዳዮች ሥራ ላይ ለማዋል በሚመለከተው አካል በሚጠየቅበት ጊዜ ድጋፍ የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

**83.የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች**

1) ይህ ደንብ ጸድቆ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት በፍርድ ቤት ክርክር ላይ ያሉ ማናቸውም ጉዳዮች ቀድሞ በነበሩ ህጎች መሰረት የሚፈጸሙ ይሆናል፡፡
2) ከዚህ በፊት የተቋቋሙ ማህበራት በዚህ ደንብ መሰረት በድጋሚ እስከሚደራጁ ድረስ ሥራቸውን የሚቀጥሉ ይሆናል፡፡

**84.መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**

ይህንን ደንብ ስራ ላይ ለማዋል ቢሮው መመሪያዎችን ያወጣል፡፡

**85.የተሻሩና ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ህጎች**

ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረን ማንኛውም መመሪያና ልማዳዊ አሰራር በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

**86. Wodho Loosu Aana Hossanno Yanna**

Tini wodho qoqqowu jefisiisanote amaale mininni kaajjitu Badheessa 8, 2017 M.D hanafe loosu aana hossanno.

**Hawassa**

**Badheessa, 2017 M.D**

**Desta Ledamo**

**Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Pirezidaante**

**86.ደንቡ ሥራ ላይ የሚውልበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ከፀደቀበት መጋቢት ፰ ቀን ፳፻፲፯ ዓ.ም ጀምሮ ስራ ላይ ይውላል

**ሀዋሳ**

**መጋቢት ፳፻፲፯ ዓ.ም**

**ደስታ ሌዳሞ**

**የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፕረዝዳንት**